*Ethiopian Journal of Behavioral Studies, 2018, 1 (1), 13-30*

# በምሥራቅ ጎጃም አካባቢ ባህላዊ የልጆች አስተዳደግ ሂደት የቀንጃ ምንነት፣ ሚና፣ ትግበራና አንድምታ

Mebrate Belachew and Belay Tefera

***አጽህሮተ ጥናት (Abstract):*** *አንድ ማህበረሰብ ሥኑ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህልውናዎቹን የሚያስጠብቅባቸውና የሚያስቀጥልባቸው ስልቶች አሉት፡፡ ከዚህ አኳያ ይህ ጥናት የተከናወነው በምስራቅ ጎጃም ዞን አንድ ማህበረሰብ ውስጥ በሚተገበር የቀንጃ ሥርዓት ምንነትና ባለው አንድምታ ላይ ነው። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት ከፊል-ነጻ ቃለ መጠይቅ፣ ሰነድ ምልከታና በግል የሚሞላ የውሎ ቅጽ በመጠቀም በዓላማ ተኮር ንሞና ከተመረጡ 21 ተሳታፊዎች አይነታዊ መረጃዎች ተሰብስበዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ካላቸው ጭብጥ ወይም በጥናቱ ከሚያሳኩት ግብ አንጻር ተደራጅተው ገላጭ በሆነ መንገድ ከቀረቡ በኋላ (1) የቀንጃ ሥርዓት ማህበረሰቡ ያለበትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ለመፍታት ሲጠቀምበት የቆየ (እየተጠቀመበት ያለ) መሆኑን፤ (2) ቀንጃ ወንዶች ብቻ የሚገቡበትና ከህጻናት በተጨማሪ አዋቂዎችም ሊገቡበት እንደሚችሉ፤ (3) ቀንጃ የራሱ የውል ኢያያዝ ሂደት እንዳለው፤ (4) ቀንጃ መግባት ለልጆችና ለቤተሰባቸውም ህልውናና ለወደፊት ኑሯቸው አስፈላጊ መሆኑንና (5) መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች ግን የቀንጃ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ለማስቀረት እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ የጥናቱ ግኝት ያሳያል። በዚህ ግኝት መሰረት ቀንጃ አስከፊ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ነው ወይስ አይደለም ብሎ መበየን የሚያስችሉ ጥናቶችን ማድረግ እንደሚያስፈልግና መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ተቋማት እየተከተሉት ያለው ቀንጃን ሙሉ ለሙሉ የማስቀረት አካሄድ (total abolitionist approach) መፈተሽ እንዳለበት የይሁንታ ምክረ-ሃሳቦች ተጠቁመዋል።*

## *መግቢያ*

አንድ ማህበረሰብ ሥነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህልውናዎቹን የሚፈታተኑ ችግሮች ሲያጋጥሙት እነዚህን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ የሚፈጥራቸው እና/ወይም በጊዜ ሂደት የሚያሻሽላቸው የተለያዩ ተግባራትና ዘዴዎች አሉት (ሲምስና ስቴፈንስ፣ 2005 እ.ኤ.አ[i])። እነዚህ ዘዴዎችና ተግባራት በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ ግለሰቦች አካላዊ፣ አስተሳሰባዊና ስሜታዊ እድገቶች ላይ ዘርፈ-ብዙ ተጽዕኖዎችን ሊያሳድሩ እንደሚችሉ በዘርፉ ላይ ትኩረት ያደረጉ ጸሀፍት አመላክተዋል (ፓፓሊያና ኦልድስ፣ 1990 እ.ኤ.አ)። በመሆኑም እነዚህ የማህበረሰብ ተግባራትና ዘዴዎች በግለሰቦች እድገት ላይ የሚያሳድሩትን አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽእኖዎች በጥናትና ምርምር ፈትሾና ለይቶ ማሳየት አዎንታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ተግባራትን ለማጎልበት እንዲሁም ጉዳት የሚያደርሱ ተግባራትንና ዘዴዎችን ደግሞ ለማስቀረት ወይም ለማስተካከል የተሻለ አማራጭ አቀራረብ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ይህ የበለጠ ትርጉም የሚኖረው ከልጆች አስተዳደግ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የልጆችን አስተዳደግ በሚመለከት አሁን አሁን እየተበራከተ የመጣ ነገር ቢኖር በተለያዩ ምክኒያቶች ልጆች ከወላጆቻቸው ውጪ የማደጋቸው ሁኔታ ነው፡፡

ልጆችን በተፈጥሮ ወላጆቻቸው አማካኝነት የማሳደግና የመንከባከብ ወይም የመደገፍ ሃላፊነትና ተግባር በተለያዩ ምክንያቶች ሲስተጓጎል ማህበረሰቡ የሚፈጠራቸው ወይም የሚያበጃቸው አማራጭ የልጆች ማሳደጊያና መደገፊያ ዘዴዎችና ሥርዓቶች በተለያዩ የሃገራችን አካባቢዎች ይገኛሉ። ከእነዚህ ሥርዓቶች መካከል በንጽጽር ሰፋ ያለ እውቅናና ትኩረት ያገኘው የጉዲፈቻ ሥርዓት ነው። ይህ ሥርዓት ወላጆቻቸውን በሞት ላጡ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ከወላጆቻቸው ጋር ሁነው ማደግ ላልቻሉ ህጻናት ከሁሉም የተሻለ ማህበረሰብ-አቀፍ የህጻናት መንከባከቢያና መደገፊያ አማራጭ ዘዴ እንደሆነ የጥናት ሪፖርቶች ጠቁመዋል (አያሌው፣ 2002 እ.ኤ.አ፣ ደሳለኝ፣ 2006 እ.ኤ.አ)፡፡

ይህ ስርዓት ከሚተገብረው ማህበረሰብ አልፎ በመደበኛው የኢትዮጵያ ህግ እውቅና ያገኘ የህጻናት መንከባከቢያና መደገፊያ አማራጭ ዘዴ ነው (ቤክስትሮም፣ 1972 እ.ኤ.አ)።

ሌላው ማህበረሰብ-በቀል ሥርዓት ደግሞ ወላጆች በሞት ሲለዩ ህጻናት ወይም ታዳጊ ልጆችን በህይወት ላሉ፣ ለሚታመኑና ቃል ጠባቂ ሊሆኑ ለሚችሉ ሰዎች የህጻናትን እንክብካቤና ድጋፍ አደራ የመስጠት ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ሐይማኖታዊ መሰረት ያለው ተግባር ነው (በላይና መብራቴ፣ በህትመት ላይ ያለ)። በአደራ ሥርዓት ሟች ወላጅ በሞት አፋፍ ላይ በደረሰ ጊዜ አደራ ተቀባዩን ሰው አስጠርቶ ስለልጆቹ የወደፊት እንክብካቤና ስለሚያወርሳቸው አንጡራ ሀብት በአካባቢው ሽማግሌዎች ወይም የሐይማኖት አባቶች ፊት "የልጆቼን ነገር አደራ በምድር አደራ በሰማይ" የሚል የኑዛዜ ቃል ያስተላልፋል (በላይ፣ 2007 እ.ኤ.አ)። የሚያጋጥሙትን ህሊናዊና ማህበራዊ ጫናዎችን ለመቋቋም ወይም ማህበራዊ ማእቀቦችን ለማስቀረት ሲል አደራ ተቀባዩ የተሰጠውን አደራ ላለማጓደል የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንደሚያደርግ በላይ (2007 እ.ኤ.አ) አያይዞ ጠቅሷል። ይህ ሥርዓት ህጻናት ወደጎዳና ኗሪነት እንዳይገቡ በመከላከል (ይግዛው፣ 2009 እ.ኤ.አ) እና የሥነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት ከሌሎች ተቋም-ተኮር የህጻናት መንካባከቢያ ዘዴዎች የተሻለ አማራጭ ሊሆን እንደሚችል (በላይና መብራቴ፣ በህትመት ላይ ያለ) ጠቁመዋል።

ሌላው የልጆች ማሳደጊያ አማራጭ ዘዴ ልጆችን ቀንጃ የመስጠት ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በተለይ በአንዳንድ የገጠሩ የአርሶ አደር አካባቢዎች የተለመደ ተግባር ነው (ሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ)። ከቃሉ ትርጓሜና አጠቃቀም ብንነሳ አምሳሉ (2002፣ ገ. 85) በአማርኛ-እንግሊዝኛ መዝገበ ቃል መጽሃፋቸው ቀንጃ የሚለውን ቃል "harness mate (plough oxen)" "አጣማጅ በሬ" የሚል አቻ ጥሬ የእንግሊዝኛ ፍች የሰጡት ሲሆን ሁለት አይነት አውዳዊ

ትርጉሞች ሊኖሩት እንደሚችሉ ደግሞ የአቢሲኒካ መዝገበ-ቃላት (2016 እ.ኤ.አ) ጠቅሷል። የመጀመሪያው ትርጉሙ ቁጥር ከመቁጠር ጋር የተያያዘ ሲሆን በጥንድ ቆጥረን አንድ ከተረፈ የተረፈውን 'ቀንጃ' እንለዋለን። በዚህ አውዱ ቀንጃ ነጠላ ወይም ያልተጣመረ፣ ለመጣመር እየጠበቀ ያለ ማለት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፡- አጣማጅ የሌለው አንድ በሬ 'ቀንጃ' ሊባል ይችላል። ይህም በብዙው የኢትዮጵያ ክፍል እርሻ ለማረስ የግድ ሁለት ወይም ጥንድ በሬዎች የሚያስፈልጉ በመሆኑ አንድ በሬ ያለው ሰው ሌላ በተመሳሳይ አንድ በሬ ያለውን ሰው ፈልጎ ማግኘትና ሁለቱ በሬዎች በጋራ ሁነው ወደ እርሻ ስለሚሰማሩ ሊሆን ይችላል። በዚህኛው ትርጉሙ ቀንጃ የሚለው ቃል 'መቀናጀ' ከሚለው ቃል ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ሶፍያና ታጠቅ (2016 እ.ኤ.አ፣ ገ.51) አስፐንን (1993 እ.ኤ.አ፣ ገ.52) ጠቅሰው መቀናጀት የሚለውን ቃል ትርጓሜ እንዲህ አስቀምጠውታል።

> *[It] is a normal means of making one t'e mad (an ox-team) by peasant households who possess only one ox since a pair of oxen is needed to plough the land. Meqenajo can also refer to arrangements normally classified as egni (labor power) or arso ('borrowing' of oxen, including rearing and feeding as well as ploughing own land and that of ox owner). (Aspen, 1993, p.52 cited in Sophia & Tatek, 2016, p.51).*

ቀንጃ '*ሥራ የሚያግዝ፣ ለመጣመር የተዘጋጀ ወይም* ለመጣመር ፍላጎት ያለው ሰው' የሚል ተጨማሪ ትርጉምም ሊኖረው ይችላል። በዚህ በሁለተኛው አውዳዊ ትርጓሜው ቀንጃ 'ህጻናት ወይም አዋቂዎች በጉልበት ሰራ መታገዝ ወደሚፈልግ ቤተሰብ ዘንድ ሂደው የሚኖሩበት፣ ሥራ የሚሰሩበት እና በስራቸው አበል የሚያገኙበት ሥርዓት' የሚል ጠቅለል ያለ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ከዚህ ጋር በተገናኘ ግዛቸው የተባለ የድረ-ገጽ ጦማሪ (blogger) እ.ኤ.አ 2012 በጡመራ ገጹ ላይ ቀንጃ ማለት "የኢኮኖሚ አቅማቸው አነስተኛ የሆኑ ወላጆች … ልጆቻቸውን [ህጻናትን] ለሌሎች ሰፊ የእርሻ መሬትና ከብት ላላቸው ሰዎች እንዲያገለግሉ በመስጠት በአመት ከሚያመርቱት ምርት በስምምነታቸው መሰረት…" የሚያገኙበት ባህላዊ ሥርዓት ነው ሲል ተርጉሞታል።

የቀንጃ ሥርዓት ያለውን ገጽታ እና በተላኪ ህጻናት እድገት ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ በሚመለከተ አንዳንድ ጸሃፍት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። ግዛቸው ከላይ በተጠቀሰው ገጹ ላይ "… [በአ]ንዳንድ ቦታዎች [የቀንጃ] ስምምነቱ የሚደረገው ህፃናቱን ልክ እንደሚሸጥ *እቃ* ወደ ገበያ ይዞ በመውጣት መሆኑ [ቀንጃ] የህፃናት *ሽያጭ* ወይም *ክራይ* ነው" *(አጽንኦት ተጨምሮበታል)* በማለት የቀንጃ ሥርዓትን ጎጅነት በአሉታዊ ገጽታው አመላክቶ ይህ ሥርዓት ሊቀር እንደሚገባ አስተያየቱን አስፍሯል። ከዚህ አስተያየት በተቃራኒው Sophia እና Tatek (2016) በአማራ ክልል አዊ ዞን አካባቢ ባካሄዱት አይነታዊ ጥናት ሪፖርታቸው ላይ የቀንጃ ሥርዓት ከላይ ወይም ከውጭ በቀላሉ እንደሚመለከቱት ሳይሆን በተጠቀሰው በአካባቢ የግብርና ሥራ ዘንድ በስፋት ያለውን የ'ጋርዮሻዊነት'ና የ'ተባባሪነት' ስርዓት የሚያንጸባርቅ እንደሆነ እንደሚከተለው አመላክተዋል።

> *It does not merely refer to a scenario whereby children are transferred [bonded] from economically poor to economically wealthy households to work; rather, it entails a wider context of 'teaming' and 'collaboration' of rural agricultural labour (Sophia & Tatek, 2016, p.51).*

ሶፍያና ታጠቅ (2016 እ.ኤ.አ) በጥናታቸው የህጻናት ቀንጃ ሥርዓት ከልጆች የአስተዳደግ ዘይቤ ጋር የተቆራኘ እና ለቀንጃ ላኪ ቤተሰቦች የኢኮኖሚ ፋይዳ እና ለተላኪ ህጻናት ደግሞ የግብርና ሥራ ክሂል በማስገኘት፣ ጠባይ በማስተካከል እና የሥነ-ልቦና የበላይነትን እና ሃላፊነትን በማስገኘት በኩል የራሱን ድርሻ እንደሚጫወት ጠቁመዋል። የቀንጃ ሥርዓት በተቀባይና ላኪ ቤተሰቦች እንዲሁም በተላኪ ህጻናት ዘንድ ሥነ-ልቦናዊና ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችን በመሸፈን አዎንታዊ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ ሥርዓቱን ሙሉ በሙሉ የማስቀረት አካሄድ (total abolitionist approach) ስህተት እንደሆነ ሶፍያና ታጠቅ አመላክተዋል። ይህም ኦርኪን (2010 እ.ኤ.አ) እንዳስቀመጠችው ከፊል የማስቀረት አቀራረብ (regulatory approach) ለቀንጃ ሥርዓት ይበልጥ የተሻለ መሆኑን የሚጠቁም ሊሆን ይችላል።

የቀንጃ ሥርዓት በህጻናት እድገት ላይ ከሚያደርሰው ጉዳት (ግዛቸው፣ 2012 እ.ኤ.አ) ወይም ከሚያስገኘው ጠቀሜታ (ሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ) አኳያ የተደረጉ ጥናትና ምርምሮች በቁጥርም ይሁን በሥፋት አናሳ መሆናቸው የቀንጃን ምንነትና በተሳታፊ ግለሰቦች በተለይ በህጻናት እድገት ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ በተገቢውና በሚፈለገው መጠን ላለመረዳት መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ። በመሆኑም ይህ ጥናት በይበልጥ ያተኮረው በቀንጃ ሥርዓት ምንነትና ባለው አንድምታ ላይ ነው። ጥናቱ በእነዚህ ዘርፎች ላይ ማተኮሩ (1ኛ) በቀንጃ ላይ ተጨማሪ ማብራሪያ ለማከል፣ (2ኛ) ቀንጃን አስመልክቶ በሚተገብረው ማህበረሰብ እና በሌሎች ተዋናይ በተለይ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ዘንድ ያለውን የአተያይ (perspective) ልዩነት ለማሳየት እና (3ኛ) ወደፊት የቀንጃ ሥርዓት በህጻናት አካላዊ፣ አስተሳሰባዊ እና ማህበረ-ስሜታዊ እድገቶች ላይ በሚያሳድረው ተጽእኖ ላይ ለሚደረጉ ጥናቶች መጀመሪያነት ሊያገለግል ይችላል። ስለሆነም በዚህ ጥናት ሶስት መሪ ጥያቄዎችን በማንሳት ምላሽ ለማግኘት ተሞክሯል።

1. የቀንጃ አተገባበር ሥርዓት ምን ይመስላል?
2. ህጻናት ቀንጃ በመግባት ሂደት ያላቸው ተሳትፎ ምን ይመስላል?
3. ህጻናት ቀንጃ በገቡበት ቤተሰብ የሚያጋጥማቸው ሁኔታ ምን ይመስላል?

በአጠቃላይ ይህ የጥናት ሪፖርት አራት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው ክፍል መግቢያ ሲሆን በዚህ ክፍል የቀንጃን ትርጓሜ፣ አጠቃቀምና ያለውን ፋይዳ ከአሁን በፊት ተጽፈው የተገኙ ጥናቶችንና መጣጥፎችን አጠናቅሯል በማጠናቀር ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህ ክፍል ይህን ጥናት ማከናወን ሊያስገኝ ስለሚችለው ጠቀሜታዎች፣ ስለጥናቱ መሪ ጥያቄዎች እና የጥናቱን ወሰን ያመላክታልለማመላከት ተሞክሯል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጥናቱ ስለተከተላቸው የአጠናን ዘዴዎች የሚያብራራ ሲሆን የጥናቱን ንድፍ፣ የጥናቱን ተሳታፊዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የአሰባሰብ ሂደቶችን እንዲሁም የመረጃ አቀራረብና አተናተን ዘዴዎችን ያሳያል። ሶስተኛው ክፍል በጥናቱ የተገኙ ውጤቶችና የውጤቶቹን ማብራሪያ ያሳውቃል። በሪፖርቱ የመጨረሻው ክፍል ደግሞ የጥናቱ መደምደሚያና የይሁንታ ሃሳቦች ተጠቁመዋል።

## የአጠናን ዘዴዎች

*የጥናቱ ንድፍ*

ሰፊና ዝርዝር ማብራሪያ በማስገኘት (ፓተን፣ 2002 እ.ኤ.አ)፣ "ያለውን ነገር እንዳለ" በመግለጽ፣ "ጠንካራ፣ ሰፊና የዳበረ ማብራሪያ" በመስጠት (ያለው 1998፣ ገ.20 እና 425) እና የተሳታፊዎችን እይታና ግንዛቤ በቀጥታ በማቅረብ (በላይና አብዲናስር፣ 2015 እ.ኤ.አ) የተሻለ ነው በማለት ይህ ጥናት አይነታዊ (Qaulitative) የጥናት ንድፍን እንዲከተል ተደርጓል። ይህም የሆነው በቀንጃ ሥርዓት ላይ የተካሄዱ የጥናት ጽሁፎችን ማግኘት አዳጋች በመሆኑ (ከሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ በስተቀር) እና በዚህም የተነሳ ለአካዳሚክ ማህበረሰቡ ስለ ቀንጃ ሥርዓት ምንነትንና በህጻናት እድገት ላይ ያለውን አንድምታ ማስተዋወቅና ሰፊ ገለጻ ማቅረብ አስፈላጊ ነው የሚል ምክንያታዊ ሀሳብ በመያዝ ነው።

*የጥናቱ ተሳታፊዎች*

የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች የሚገኙት በወይራ ቀበሌ ነው። ይህ ቀበሌ በሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም ዞን እነማይ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ380 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል። በዚህ ቀበሌ የሚኖሩ አብዛኛው የማህበረሰብ አባላት ዝናብን መሰረት ባደረገ ባህላዊ የእርሻ ስራ ይተዳደራሉ (ቃለ-መጠይቅ፣ የአካባቢው ግብርና ባለሙያ፣ ግንቦት 2008 ዓ.ም) ።

ለዚህ ጥናት ሁለት አዛውንት ሽማግሌዎች፣ አምስት ቀንጃ የላኩ ወላጆች፣ አምስት ቀንጃ የተቀበሉ (ያስገቡ) አባወራዎች፣ አምስት በአሁኑ ሰዓት ቀንጃ የገቡ ህጻናት እና ሁለት ቀንጃ ገብተው የነበሩ አዋቂዎች እና ሁለት ከመንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅት ተወካዮች በድምሩ 21 ግለሰቦች ተሳታፊ ሁነዋል። እነዚህ ተሳታፊዎች ሲመረጡ አላማ ተኮር (Purposive) ወሳኝ ናሙና (Nonprobability sampling) ዘዴ በተግባር ላይ ውሏል። ይህም ስለቀንጃ ሥርዓት በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ የታሰቡትን እና በመስክ መረጃ ስብሰባው ወቅት (ማለትም ግንቦት 2008 ዓ.ም የመጀመሪያ ሳምንት) የተገኙትን በመስፈርትነት በመጠቀም ነው።

*የመረጃ መሠብሠቢያ መሳሪያዎችና የመረጃ አሠባሠብ ሂደት*

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከፊል-ነጻ ቃለ መጠይቅ (Semi-structured interview)፣ የሰነድ ምልከታ እና በግል የሚሞላ የውሎ ቅጽ (Self-filled chores form) ተግባር ላይ ውለዋል። በእነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ዝግጅት ወቅት የቀንጃን ሥርዓት በሚመለከት ሊታወቁ ይገባቸዋል የተባሉ እና በቀንጃ ተግባር ውስጥ የልጆችን አያያዝ ሁኔታ የሚመለከቱ ነጥቦች በማንሳት እንዲሁም በቀንጃ ሥርዓት ዙሪያ የተጻፉ ሪፖርቶችን (ለምሳሌ፡- ሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ) በመዳሰስ ሁለቱ አጥኝዎች እርስ በእርሳቸው እንዲሁም ከሌሎች ሙያተኞች ጋር ውይይት ተደርጓል።

ስለሆነም በቃለ-መጠይቁ ቀደም ሲል የነበረውን የቀንጃ አተገባባር፣ የቀንጃን ውል አያያዝ፣ ቀንጃ የሚገቡ ህጻናት ዝቅተኛ እድሜን፣ ቀንጃ የገቡ ህጻናት ቀንጃ በገቡበት ቤተሰብ የሚያጋጥማቸውን ሁኔታ እና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የተብራራ ምላሽ ከተሳታፊዎች ማግኘት ተችሏል። በተጨማሪም መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች በቀንጃ ዙሪያ እያከናወኗቸው ያሉ ተግባራትን ለማወቅ ሲባል የሰነድ ምልከታው አገልግሎት ላይ ውሏል። እንዲሁም ሃሳባቸውን በጽሁፍ ማስፈር ይችላሉ ተብለው የታሰቡ ቀንጃ የገቡ ህጻናት በቀን ውስጥ በመደበኛነት የሚያከናውኗቸው ተገባራትን እንዲዘረዝሩ በግል የሚሞላውን ቅጽ ወደ ቤታቸው ወስደው እንዲሞሉ ተደርጓል (ይህ ዘዴ በታጠቅ፣ 2010 እ.ኤ.አ ተሞክሯል)።

በመረጃ ስብሰባው ወቅት ተሳታፊዎችን ለመለየትና ከአንደኛው አጥኝ ጋር ለማግባባት፣ በቃለ-መጠይቁ ወቅት በተሳታፊዎችና በአጥኝው መካከል የነበረውን ተግባቦት ለማሰናሰን ጥናቱ የተከናወነበት ቀበሌ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ[ii] እንዲሳተፍ ተደርጓል። የመረጃ ስብሳባ ሂደቱን ለማቀላጠፍ እና ለትንተና ዝግጁ ለማድረግ ሲባል ሰፋ ያለ የጽሁፍ ማስታወሻ በቃለ መጠይቁ ወቅት ተይዟል፡፡ እንዲሁም ከእያንዳንዱ ተሳታፊ የተገኙ መረጃዎች በመረጃ ስብሰባው ወቅት ለማፍታታት ተሞክሯል።

*የጥናቱ መረጃ አተናተን እና አቀራረብ ዘዴዎች*

ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት አይነታዊ መረጃዎች አቀራረብና አተናተን ሂደት ሶስት ደረጃዎችን እንዲያልፍ ተደርጓል (ማይልስና ሁበርማን፣ 1994 እ.ኤ.አ)። የመጀመሪያው ደረጃ መረጃ 'መቀነስና መጭመቅ' ሲሆን ከተሰበሰቡት አጠቃላይ መረጃዎች ውስጥ ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ ከማያስፈልገው የመለየት ተግባር ተከናውኗል። ከዚህ በመቀጠል መረጃ 'የማሳየት' ሂደት የተከናወነ ሲሆን የተለዩት መረጃዎች ትርጉም ባለው መንገድ ተተንትነው እንዲቀርቡ ሁነዋል። በመሆኑም እነዚህ መረጃዎች ካላቸው ጭብጥ (ያለው፣ 1998) ወይም በጥናቱ ከሚያሳኩት ግብ (በላይና አብዲናስር፣ 2015 እ.ኤ.አ) አንጻር እንዲደራጁና ገላጭ በሆነ መንገድ እንዲቀርቡ ተደርጓል። በመጨረሻም ጥናቱ ያነሳቸው መሪ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሲባል የተሰበሰቡት መረጃዎችን 'ማጠቃለያ የመስጠት' ሙከራ እና በዚህም መሰረት በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ እንዲታከልበት ተደርጓል።

## የጥናቱ ውጤትና ማብራሪያ

*የተሳታፊዎች ዳራዊ መረጃ*

በዚህ ጥናት በቀንጃ ውስጥ በቀጥታ ተሳታፊ የሆኑ (ቀንጃ የገቡ ህጻናት፣ ቀንጃ የተቀበሉና የላኩ) እና ስለቀንጃ ማህበረ-ባህላዊ አመጣጥና አተገባበር የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው (ሽማግሌዎች፣ ከአሁን በፊት ቀንጃ ገብተው የነበሩና መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ) አካላት ተሳትፈዋል። በሠንጠረዥ 1 የእነዚህ ተሳታፊዎች ብዛት፣ ጾታ እና እድሜ ተጠቅሷል።

**ሠንጠረዥ 1 የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃ**

| *የተሳታፊዎች ምድብ* | *ብዛት* | *ጾታ* | *እድሜ* |
|---|---|---|---|
| አዛውንት ሽማግሌ | 2 | ወንድ | 68 እና 71 ዓመት |
| ቀንጃ ላኪ | 5 | 4 ወንድና 1 ሴት | ከ41 እስከ 67 ዓመት |
| ቀንጃ ተቀባይ | 5 | ወንድ | (የተሳተ መረጃ ) |
| ቀንጃ የገቡ ህጻናት | 5 | ወንድ | ከ12 እስከ 16 ዓመት |
| ቀንጃ ገብተው የነበሩ አዋቂዎች | 2 | ወንድ | 34 እና 28 ዓመት |
| መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች | 2 | ወንድ | (የተሳተ መረጃ) |
| **ድምር** | **21** | | |

**ሠንጠረዥ 1** እንደሚያሳየው በዚህ ጥናት በቀንጃ ሥርዓት ውስጥ ቀጥኛ የሆነ (ማለትም ቀንጃ ላኪና ተቀባይ ቤተሰቦች እና የተላኩ ህጻናት) እና ቀጥተኛ ያልሆነ (ማለትም ሽማግሌዎች፣ ቀንጃ ገብተው የነበሩ እና መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ) ተሳትፎ ያላቸው ግለሰቦች ተሳትፈዋል።

### *የቀንጃ ሥርዓት አተገባበር*

*ቀደም ሲል የነበረውና በአሁኑ ጊዜ ያለው የልጆች ቀንጃ አተገባበር*

የቀንጃን አመጣጥ ሊጠቁም ይችላል በሚል የጥናቱ ተሳታፊ ሽማግሌዎች በአሁኑ እና ቀደም ባሉት ጊዜያት ስለነበረው የቀንጃ አተገባበር ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው የሚከተለውን ብለዋል።

ጠያቂ:- *እርስዎ ልጅ በነበሩበት ጊዜ እና በአሁኑ ጊዜ ቀንጃ የሚገቡ ልጆች ብዛት እንዴት ያዩታል? … ማለቴ ቀንሷል ወይስ ጨምሯል?*

መላሽ$_1$:- *አይ … [ግንባራቸውን በእጃቸው ጣት እየዳሰሱ] አሁንማ አይፈልጉት።*

ጠያቂ:- *'አይፈልጉት' ሲሉ …?*

መላሽ$_1$:- *በእኛ ግዜ'ማ [ከ50 እስከ 60 ዓመታት በፊት] እንዳው ተቤተሰቦቻቸው ትንሽ ተተቸገሩ ታለው ዘንድ ቀንጃ መሀድ ልማድ ነበረ።*

ጠያቂ:- *አሁንስ?*

መላሽ$_1$:-*ያሁን'ማ ልጆች ተስንት አንድ ነው ቀንጃ እሚሀዱ።*

ጠያቂ:- *ይህ የሆነው ለምን ይመስለዎታል?*

መላሽ$_1$:- *ለምን'ማ … ያአሁን ዘቨን ልጆች በረው እሚሃዱ ተከተማ፣ ቀንጃን መች ተጉዳይ ይጥፉታል።*

ጠያቂ:- *ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ቀንጃ መግባት ቀርቷል ማለት ነው?*

መላሽ$_1$:- *አይ እሱማ እንዲያ በኛ ግዜ እንደነበረው አደለም ማለቴ ነው'ንጅ አንዳንዶች አሁንም ይገባሉ። ቀንጃ ፈላጊውማ አሁንም ብዙ ነው። ግን [ቀንጃ] እሚገባ ተሄት ተግኝቶ።*

ከላይ ከቀረቡት ነጥቦች ጋር በተያያዘ የሁለተኛው አዛውንት ሽማግሌ ቃለ-ምልልስ ደግሞ እንደሚከተለው ይቀርባል።

ጠያቂ:- *ቀንጃ የሚገቡት ልጆች ብዛት ከድሮና ከአሁን የትኛው ይሻላል?*

መላሽ$_2$:- *የድሮው ይበዛል ባይ ነኝ። ያውም እ'ንዲህ እንዳሁኑ ሰው ባልበዛበት ግዜ። ድሮማ ጥሪት የሌለው ሚላስ ሚቀመስ [የሚመገበው] የሌለው ቤት ልዡን ተቀንጃ ይልክና ባ'መቱ እህል ያመጣለታል።*

ጠያቂ:- *አሁን ያሉት ልጆች ቀንጃ አይገቡም ማለት ነው?*

መላሽ$_2$:- *እሱማ ይገባሉ። ግን ፈላጊው በዝቶ ቀንጃ የሚገባ ልዥ ሰው በሰው ታልሆነ አይገኝም።*

ጠያቂ:- *ቀንጃ የሚገባ ልጅ የጠፋበት ምክንያት ምን ይመስልዎታል?*

መላሽ$_2$:- *እንዲያው ጉብሉ [ህጻኑ] ገና በሁለት እግሩ መሄድ ሲጀምር 'ወደ ተማሪ ቤት' ነው ሚባለው። መማራቸው ባልከፋ ግን ተተቸገሩ ቀንጃ ገብቶ ማደግ ይሻላል።*

እነዚህ ምልልሶች እንደሚያመለክቱት ቀደም ባሉ ጊዜያትም ቀንጃ መግባት የሚፈልጉ ልጆች መኖራቸውን ነው። ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት ቀንጃ ማስገባት የሚፈልጉ ቤተሰቦች ቢኖሩም ቀንጃ መግባት የሚፈልጉ ልጆች ብዛት እንደበፊቱ ሁሉ እምብዛም አይደለም። በተጨማሪም በአሁኑ ሰዓት ያሉ

ልጆች ሥራ ለማግኘትና ለመስራት ለመረጃዎች ቅርብ በመሆናቸው አማራጫቸው ከበፊቶቹ ልጆች የሰፋ ነው።

በዚህም መሰረት ቀንጃ በአሁኑ ሰዓት እየተተገበረ ያለ ስርዓት ቢሆንም ቀንጃ መግባት የሚፈልጉ ልጆች ቁጥር ከቀድሞዎቹ ጊዜ ያነሰ መሆኑንና ለዚህም ዋና ምክንያቶች የከተሞች መስፋፋት ለልጆች የተሻለ የገቢ አማራጮችን ስለሚያመቻችላቸው የልጆች ወደ ከተማ መንቀሳቀስ (መሰደድ) እና ልጆች ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት እንዲገቡ መደረጉ (መገደድ) መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### *ቀንጃ በጾታ የተገደበ እና በእድሜ የተለያየ ስለመሆኑ*

ቀንጃ ከጾታ እና ከእድሜ ጋር ያለውን ተዛምዶ ሁለቱ ሽማግሌዎች የሚከተሉትን ሃሳቦች ሰንዝረዋል።

> *ጠያቂ፡- ከወንድና ከሴት ልጆች ብዙ ጊዜ ቀንጃ የሚገባው ማን ነው?*
>
> *መላሽ$_2$፡- ወንድ ነው ቀንጃ እሚገባ፡፡ ሴት እንዲውም ቀንጃ አትገባም፡፡ ወንድ ተልኧንቱ ጀምሮ አዋቂም ቢሆን ሃብት ንብረት ለማግኘት ተፈለገ ቀንጃ ሊገባ ይችላል።*
>
> *ጠያቂ፡- የአዋቂዎችና የልጆች ቀንጃ አገባብ አንድ አይነት ነው?*
>
> *መላሽ$_2$፡- አገባባቸውም ለየቅል ነው። ቀንጃ ሚገባው አዋቂ ተሆነ ቀንጃ ተገባበት ተያንዳንዱ ያዝመራ አይነት ይካፈላል። ቀንጃ ሚገባው ጉብል [ህጻን] ተሆነ ግን ቀንጃ ተገባበት ቤት በቁርጫ እህል ወይም ገንዘብ ይወስዳል።*
>
> *ጠያቂ፡- ሴቶች ቀንጃ ይገባሉ?*
>
> *መላሽ$_1$፡- የለም። የሴት ቀንጃ የለም።*

ቀንጃ የሚገቡት ወንድ ልጆች ብቻ መሆናቸውን እና ከህጻናት በተጨማሪም አዋቂዎችም (adults) ቀንጃ እንደሚገቡ ከላይ የቀረቡት ቃለ ምልልሶች ጠቁመዋል።

ሴቶች ቀንጃ የማይገቡባቸውን ምክንያቶች የቀረቡት መረጃዎች ባያሳዩም ጥናቱ በተከናወነበት ማህበረ-ባህል ሥርዓት መሰረት ቀንጃ መግባት የወንዶች ብቻ ተግባር እንደሆነ መረዳት ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ ቀንጃ ለመግባት ዝቅተኛው የህጻናት እድሜ በዚህ ጥናት ባይታወቅም በቤት ውስጥ ካሉ የግብርና ሥራዎች ውስጥ በህጻናቱ የእድገት ደረጃ ሊሰሩ የሚችሉ ስራዎች እስካሉ ድረስ ቀንጃ ሊገቡ እንደሚችሉ መረዳት ይቻላል። ይህም ከልጅነት ዘመን ማህበረ-ባህላዊ ጽንሰ-ሃሳቦች (conceptions of childhood) ጋር ሊዛመድ ይችላል። ማለትም ማህበረሰቡ በልጅነት ዘመን እንዲከናወኑ የሚጠብቃቸው አብዛኛው ተግባራት (developmental tasks) ህጻናት ባላቸው እድሜ ሳይሆን በሚያሳዩት አካላዊ፣ አስተሳሰባዊ እና ማህበረ-ስሜታዊ ሁኔታዎች በመሆኑ ነው (ፖሉሃ፣ 2007 እ.ኤ.አ)። በገጠሩ ማህበረሰብ አካባቢ ህጻናት እድሜያቸው አምስት ዓመት ሲሞላቸው ጀምሮ የተለያዩ የቤት ውስጥ ተግባራትን (ለምሳሌ፡- እንስሳትን መጠበቅ፣ ሌሎች ህጻናትን መንከባከብ) እንደሚያከናውኑ የተለያዩ የጥናት ሪፖርቶች ጠቁመዋል (አሰፋና በዲ፣ 2003፤ ጌትነትና በልዩ፣ 2012; ኦርኪን፣ 2012 እ.ኤ.አ)። ግዛቸው (2012 እ.ኤ.አ) ዝቅተኛው የቀንጃ መግቢያ እድሜ ሰባት ዓመት እንደሆነ ቢጠቅስም ዝቅተኛው የቀንጃ መግቢያ እድሜ እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ካለው የልጅነት ዘመን ማህበረ-ባህላዊ ጽንሰ-ሃሳቦች መገመት አያዳግትም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ከቀንጃ የሚገኘው አበል ከእድሜ ጋር አብሮ እንደሚጨምር ወይም አዋቂዎች ከህጻናት የተሻለ እንደሆነ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት ይቻላል። ይህም አንዳንድ የጥናት ሪፖርቶች (አሰፋና በዲ፣ 2003፤ ጌትነትና በልዩ፣ 2012; ኦርኪን፣ 2012 እ.ኤ.አ) እንደጠቆሙት ህጻናት በቤት ውስጥ ያላቸው የስራ ድርሻ እና አስተዋጽኦ ከእድሜያቸው ጋር አብሮ ስለሚያድግ ሊሆን ይችላል።

### *የልጆች ቀንጃ አይነቶች*

ቀንጃ ተቀባዩ ቤተሰብ ቀንጃ የሚያስገባው በቤተሰቡ ውስጥ ያለውን ሥራ ለማከናወን ተጨማሪ የሰው ሃይል በማስፈለጉ ወይም የተቀባዩ ቤተሰብ አባላት የየስራ ድርሻቸውን ባለመስራታቸው ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የቀንጃን አተገባበር አስመልክቶ በቀረቡት መግለጫዎች ተገልጿል። ቀንጃ ላኪ ቤተሰቦች ደግሞ ልጆቻቸውን ወደ ቀንጃ የሚልኩባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከጥናቱ ተሳታፊዎች ቃለ መጠይቅ ለረዳት ይቻላል። ስለሆነም ከሚላኩበት ምክንያት አኳያ በድህነት ምክንያት፣ በልጆች አነሳሽነት፣ ክሂል ለማግኘት፣ ሥነ-ምግባርን ለማረም የሚገባ ቀንጃ ብሎ በአራት አይነት ከፋፍሎ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል።

#### *ሀ) በድህነት ምክንያት የሚገባ ቀንጃ*

ቀንጃ ሰጪ ቤተሰቦች የሚመገቡት ምግብ ሲያጡ ወይም እጥረት ሲያጋጥማቸው ልጃቸውን ቀንጃ ልከው ልጁም ኑሮው በተሻለ ቤተሰብ የተሻለ ምግብ እና ልብስ እንዲያገኝ ለላኪ ቤተሰቡም እህል ወይም ገንዘብ እንዲያመጣ በሚል ምክንያት ሊሆን ይችላል። በዚህም ከአንድ ቤተሰብ በተለይ የላኪው ቤተሰብ ያሉትን ልጆች ማሳደግ የማይችል ከሆነ ሁለትና ከዚያ በላይ ልጆች ቀንጃ ሊላኩ እንደሚችሉ ከዚህ ቀጥሎ ያሉት መላሾች ይጠቁማሉ።

> *ልጄን ቀንጃ ያስገባሁት ተኛ ጋር እዚህ ተሚቸገር በጉልበቱ ሰርቶ እንዲለወጥ ብየ ነው። እኔ እና እናቱ ጤና አላደርገንም።… ሰው ጤና ታለው እኮ ታለው ዘንደ ተጠግቶ በጉልበቱ ሰርቶ ኑሮውን ይለውጣል። የኔም ልጅ ቀንጃ የላክሁት አሁን እሚበላው፣ እሚጠጣው [እና] እሚለብሰው ሳይቸገር ወደፊት ወረት [መነሻ ካፒታል] ይይዛል ብየ ነው። (መላሽ$_4$)*
>
> *[ልጄን] ቀንጃ ያስገባሁት የተሻለ ኑሮ እንዲኖረው ነው። ተሁለት ዓመት በኋላ ዘጠነኛ ክፍል ስለሚገባ ቀንጃ በገባበት ተዘጠኝ በላይ ትምርት ቤት ስላለ ትምርቱን እዚያው እንዲማር በየ ነው። … እኛ*

*የትምርት ወጪውን ስለማይሆንልን ቀንጃ ገብቶ ሳይቸገር እንዲማር ብየ ነው።... እና ሺጋ ነው ... ልጄ ተመችቶት ነው እሚኖር። (መላሽ3)*

*[የእርሻ] መሬት የለንም። ትልቁና ትንሹ ልጆቼን ቀንጃ ልኬ በዓመት ትንሽ እህልና ገንዘብ ያመጣሉ። (መላሽ5)*

ቀንጃ ገብተው በሚያገኙት ገንዘብ ወይም እህል ቤተሰቦቻቸውን በመደገፋቸው ማህበራዊ ሃላፊነት የመወጣት ስሜት እንደሚሰማቸው ቀንጃ የገቡ ልጆች አስተያየታቸውን አክለዋል።

*ቀንጃ ገብቼ የማገኘውን እህል ስልክላቸው ደስ ይለኛል። (ምላሽ16)*

*ለታናሽ ወንድሜ ይኔፎርም ያሰፋሁለት እኔ ነኝ። ትልቅ ወንድሙ ነኝ... [ስለዚህ] እኔ ታላሰፋሁለት ማን ያሰፋለታል? (ምላሽ14)*

ከዚህ በላይ ከቀረቡት መላሾች መረዳት የሚቻለው ህጻናት ቀንጃ የሚላኩት የእነሱ እና የቤተሰቦቻቸው ደህንነት (wellbeing) ከአደጋ ለማውጣት ወይም ለመከላከል እንደሆነ እና ይህን ማድረጋቸው ለማህበረዊ ስብዕናቸው መጎልበት አስተዋጽኦ እንዳለው ነው።

### ለ) በልጆች አነሳሽነት የሚፈጸም ቀንጃ

አንዳንድ ቤተሰቦች የሚመገቡት ሳያጡ ወይም ሳይቸገሩ ልጃቸው "ቀንጃ ልግባ" የሚል ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። ይህም የሚሆነው የጠያቂው ቤተሰብ በየዓመቱ ከሚያመርተው ምርት ተከፍሎ አበል እንዲሰጠው ወይም እንዲታሰብለት ሲፈልግ ነገር ግን ቤተሰቡ ለዚህ ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እንደሆነ የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። በዚህ ሁኔታ ቀንጃ የገባ ልጅ በየአመቱ ቀንጃ ከገባበት ቤተሰብ የሚያገኘውን አጠራቅሞ የግሉን ንብረት ማከማቸት እንደሚጀምር ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የቃለ መጠይቅ ሃሳብ ያስረዳል።

*የእኔ እናትና አባት አርሰው ተሚያመርቱት ባመት ባመት በቁርጫ አስቡልኝ ብላቸው እምቢ በማለታቸው ነው ቀንጃ የገባሁ። ትምርቱ እምቢ ሲለኝ [ከ8ኛ ወደ 9ኛ ክፍል ለማለፍ የሚሰጠውን ክልላዊ ፈተና አላለፈም] ግዜ ንግድ ብነግድ ይሻለኛል። ... ለመነገጃ የሚሆን ወረት [መነሻ ከፒታል] ........ ቀንጃ ገብቼ ባመት ተማገኛት አጠራቅሜ [አገኛለሁ]። ቀንጃ ተገባሁ ሁለት ዓመቱ ነው። አሁን በአብቁተ [አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም] 3000 ብር አስቀምጫለሁ። ተዚህ በኋላ ሁለት ዓመት ቀንጃ ብቆይ መነገጃ እሚሆን ይበቃኛል። (መላሽ13)*

ስለሆነም ህጻናት ቀንጃ የሚገቡት የእለት ጉሳቸውን ለማሟላት ብቻ ሳይሆን ወደፊት ለሚኖራቸው ኑሮ መሰረት መጣያ የሚሆን ንብረት ለማፍራት ጭምር እንደሆነ ከዚህ የቀንጃ አይነት መገንዘብ ይቻላል።

### ሐ) የህይወትና የሥራ ክሂል ለመቅሰም የሚገባ ቀንጃ

በአንዳንድ ቤተሰቦች ዘንድ ደግሞ ቀንጃ የሚላከው ልጁ ወደፊት ለሚኖረው የግል ህይወቱ የስራና የኑሮ እውቀትና ክሂል እንዲያገኝ በሚል ምክንያት ሊሆን ይችላል። አብዛኛው የዚህ አይነት ቀንጃ ላኪ ቤተሰቦች የሚመሩት ባለቤታቸው በሞቱባቸው እናቶች ሲሆን የእርሻ መሬት እና በሬ እያላቸው ነገርግን ይህን በአግባቡ የሚያስተዳድር የቤተሰብ አባል ሳይኖር ሲቀር ልጃቸውን ቀንጃ ልከው መሰረታዊ የግብርና ሙያ እውቀትና ክሂል እንዲያገኝ የሚተገበር እንደሆነ ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው ሃሳብ ይጠቁማል።

*አባቴ የሞተው ህጣን [ህጻን] ሳለሁ ነበር። እናቴ መሬቱን የሚያዘምርላት ስላጣች እኔን ወደቀንጃ ላከችኝና ሙያ ተምሬ መጣሁ። ያለንን መሬት በበሬዎቻችን እያዘመርሁ ለእኔም የተወሰነ እያተቆረጠልኝ ራሴን ቻልሁ። ... አሁን የግሌን ቤተሰብ መስርቼ እያኖርሁ ነው። (መላሽ19)*

ይህም የገንዘብ ወይም የሃብት እጥረት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊ የህይወትና የሥራ ክሂሎችን ለመቅሰም ተብሎ ህጻናት ቀንጃ ሊላኩ እንደሚችሉ ሊያሳይ ይችላል።

### መ) የልጆችን ሥነ-ምግባር ለማረም የሚገባ ቀንጃ

ልጆች በቤት ውስጥ በተደጋጋሚ ጥፋት አጥፍተው በቤተሰቡ ውስጥ ችግር የሚፈጠሩ ከሆነ እንዲታረሙ በሚል ቀንጃ እንዲላኩ ሊደረግ እንደሚችል አንደኛው የጥናቱ ተሳታፊ ጠቁመዋል።

*ልጆች በቤት ውስጥ እረባሽ ተሆኑ፣ ሥራ የማይሰሩ [እና] ጠባያቸው የተበላሸ ተሆነ ቀንጃ ይላካሉ። ቀንጃ ያው የሰው ቤት ስለሆነ እንደነሱ ቤት አያቀብጣቸውም። [ስለዚህ[ በጠባያቸው ይገራሉ፣ ሙያም ተምረው ይመጣሉ። በዚህ መንገድም [ከቀንጃ ሲመለሱ] በቤት ውስጥ ሰጥ ለጥ ብለው [ታዛዥ] ተቤተሰቡ ጋር መጥነው ይኖራሉ ማለት ነው። (መላሽ2)*

ስለሆነም ቀንጃ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሶስት ዋና ዋና ምክንያቶች በተጨማሪ 'የአጥፊ' ህጻናት ጸባይ ማረሚያ (conduct correction) ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል።

## የልጆች ቀንጃ ውል አያያዝ ሥርዓት

ቀንጃ ሲገባ ውል እንዴትና በምን መልኩ እንደሚያዝ የጥናቱ ተሳታፊዎች ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር። በዚህም መሰረት ቃለ መጠይቅ ከተደረጉት አዛውንት ሽማግሌዎች አንዱ የሚከተለውን ብለዋል።

*ጠያቂ፦ ቀንጃ ሲገባ ስምምነታቸውን በምን መልኩ ነው የሚይዙት?*

*መላሽ1፦ አሁን አሁን ተጥፎ ነው እሚያዘው። ቀደም ግን ዝም ብሎ ይሄን ያህል ትሰጠኛለህ እስጥሀለሁ ተባብለው ነበር በእምነት ቀንጃ የሚገቡት።*

ከዚህ ምላሽ እንደምንረዳው አሁን አሁን ቀንጃ ሲገባ በቀንጃ ገቢው (ላኪው)ና በቀንጃ ተቀባዩ ግለሰቦች (ቤተሰቦች) መካከል የጽሁፍ ውል ስምምነት መያዝ እየተለመደ መምጣቱን እና ይህም በተዋዋዮች መካከል ሊኖር የሚችለውን የመካካድ ጥርጣሬ ለመቀነስ የተወሰደ መፍትሄ መሆኑን ነው።

የጽሁፍ ውሉ ከመያዙ በፊት እና ከተያዘ በኋላ ሌሎች ተግባራት በሁለቱ ቤተሰቦች አማካኝነት እንደሚፈጸሙ የጥናቱ ተሳታፊዎች ጠቁመዋል። እነዚህን ተግባራት ከቀንጃ ቀጥኛ ተሳታፊዎች (ማለትም ቀንጃ ካስገቡና ከላኩ ቤተሰቦች እና ቀንጃ ከተላኩ ልጆች) ጋር በተደረጉ ቃለ መጠይቆች ላይ በመመስረት በሶስት ምዕራፎች (እነርሱም፡- (1) ፈላጊና ተፈላጊ መገናኘት፣ (2) የግምገማና የፍተሻ ጊዜ እና (3) የውል መያዣ ጊዜ) ከፋፍሎ እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል።

**(1)** ***ፈላጊና ተፈላጊ መገናኘት፡-*** ቀንጃ የሚሰጥ ቤተሰብ ልጁን ቀንጃ መላክ እንደሚፈልግና ቀንጃ የሚቀበል ቤተሰብ ደግሞ ቀንጃ ማስገባት እንደሚፈልግ በጎረቤት እና በአካባቢያቸው ላሉ ሰዎች ይናገራሉ። ጉዳዩን የሰሙ ሰዎች በተለያዩ ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ባላቸው ስብሰባዎች (ለአብነት ለመጥቀስ ያህል እድር፣ የጽዋ ማህበር፣ ሰንበቴ፣ እቁብ፣ ሸሃ፣ ደቦ፣ ወንፈል፣ ሰርግ) ላይ ሲገናኙ መረጃዎችን ይለዋወጣሉ። በዚህ ሁኔታ መረጃው ይሰራጫል። በአሁኑ ሰዓት ቀንጃ የላኩ ቤተሰቦች ልጃቸውን ቀንጃ ለመላክ ሲያስቡ መረጃውን እንዴት እንዳስተላለፉ ከተናገሩት መካከል፡- ልጄን ቀንጃ እንደማስገባ የተናገርሁት፡-

> *የሚካሄልን ማሽር ስንጠጣ ለአንድ ወዳጄ ነበር። (መላሽ$_3$)*
> *ከቃብር መልስ እድር ተቀምጠን ስናወጋ ለ … [ስም ጠቅሰው] ነበር። (መላሽ$_4$)*

> *ሰርግ ተጠርቼ ከወትሮ ወዳጄ ጋር ስንጫወት ነበር፣ … ሌላ ግዜ ደ’ሞ ሰንቨቴ ተቀምጠን ስንጫወት ነበር። (መላሽ$_5$)*

> *እኔ ሳልሆን እናቱ [ባለቤታቸውን ማለታቸው ነው] የጥጥ እቁብ ላይ ነው። (መላሽ$_6$)*

> *የከብት ሸሃ ተራ ስንደለድል ነበር። (መላሽ$_7$)*

መረጃውን ያገኘ ቀንጃ ተቀባይ ቤተሰብ ቀንጃ ይገባል ስለተባለው ልጅ እድሜ፣ የጤና ሁኔታ፣ አካላዊ ጥንካሬ እና ባህሪ አጣርቶ ለሚፈለገው ሥራ ብቁ ከሆነ ቀንጃ ሰጪ ቤተሰብን ልጃቸውን ቀንጃ እንዲሰጡት ይጠይቃል። ከዚህ በፊት በነበረው ንኡስ ርእስ ላይ እንደተጠቆመው ዝቅተኛው የቀንጃ መግቢያ እድሜ ባይታወቅም ቀንጃ የሚገባው ልጅ ሥራ መስራት (ለምሳሌ ጥጃ፣ በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ አህያ፣ … ወዘተ መጠበቅ) ከቻለበት ጊዜ አንስቶ ቀንጃ መግባት ሊጀምር ይችላል።

> *ከብት የሚያስወጣ የሚያስገባልን ጉብል [ልጅ] አጠን ለማግኘት ቡዙ ማሰንሁ [ለፋሁ]። ተሶስት ወር በፊት ይህን አሁን ያየነውን ልዥ አገኘሁ። የልዡ እድሜ 12 ዓመት ይሆነው ይሆናል። ጠንካራ ልዥ ነው። መጀመሪያም ቀንጃ ይገባል ተብሎ ስሰማ የጠየቅሁ የልጁን እድሜ እና ጥንካሬ ነበር። (መላሽ$_8$)*

> *ርሻው አልሆን ሲለኝ ግዜ ፍየሎችን እያረባሁ ነው። ነጋ ጠባ ተፍየል ጋር መሯሯጥ ሲቸግረኝ ግዜ ፍየል የሚጠብቅልኝ ልዥ ፈልጌ ይህን ልዥ ቀንጃ ታስገባሁ ይኅው ግንቦት ቢመጣ ሁለት ዓመቱ። አሁን ልጁ እድሜው 14 ቢሆነው ነው። ከ’ናቱ ዘንድ ሳመጣው ሙሉ ጤነኛ እንዲሆን ነበር ምፈልገው አሁንም ጥሩ ወፈጥ [ጉልበተኛ] ልዥ ሁኗል። (መላሽ$_9$)*

> *እንደልቤ ላዝዘው የምችል እድሜው ልዥ የሆነ ቀንጃ እፈልግ ነበር። ታለፈው ነሐሴ ጀምሮ ከብት እሚጠብቅልኝና እሚለባኝልኝ [የሚንከባከብልኝ] ይህ ልዥ ነው። እግሩን ባለፈው የጥቅምት ገብሬል ወድቆ ወለምታ ነው መሰለኝ ትንሽ እያመመው ነው‘ንጂ በከብቶች በኩል አርፈናል ቀጥ [በትክክል] አርጎ ይዞልናል። ታገሩ ሳመጣው እጁ የማይወሳልት [የማያጭበረብር] እንዲሆን ነበር ፍላጎቴ። የዚህ ልጅ እጅም ነሻይ [የማይሰርቅ] ነው። (መላሽ$_{10}$)*

የቀንጃ አጠያየቅ በሰጭውና በተቀባዩ ቤተሰብ መካከል እንዳለው ግንኙነት ወይም የቦታ ቅርበትና ርቀት ሁኔታ በሁለት አይነት መንገድ ሊከናወን ይችላል። ሁለቱ ቤተሰቦች ቀንጃ ለመስጠትና ለመቀበል ከመፈለጋቸው በፊት የሚተዋወቁ ከሆነ ወይም የሚኖሩበት አካባቢ የተቀራረበ ከሆነ የተቀባዩ ቤተሰብ አባወራ በቀጥታ የሰጭውን ቤተሰብ ይጠይቃል። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሁለቱ ቤተሰቦች በቦታ የሚራራቁ ወይም የማይተዋወቁ ከሆነ ቀንጃ ተቀባዩ ቤተሰብ አባወራ ቀንጃ ሰጭውን ቤተሰብ ወይም አባወራ የሚግባባ ሌላ ሰው ይዞ ጥያቄውን ያቀርባል። ይህም የሚሆነው ተቀባይነትንና ተአማኒነትን ለመጨመር ሲባል ነው።

> *ተልዡ ቤተሰቦች ጋራ ኩታ ገጠሞች [ድንበርተኛ] ነን። [ሰው ሳልይዝ] … ልዣቸውን ቀንጃ እንዲሰጡኝ ጠየቅኋቸው። (መላሽ$_{12}$)*

> *የልዡንም ቤተሰብ አላውቃቸውም ነበር። እዚህ እኛ ደብር ዋይታ ተቀምጠን ስናቧልት [ስንነጋገር] ተልዡ አገር የመጣ ዋይተኛ ቀንጃ የሚገባ ልዥ እንዳለ ሲናገር ሰምቼ ልዡን ቀንጃ እንዲሰጡኝ የጠየቅሁ በዚህ ሰውየ በኩል ነበር። (መላሽ$_{10}$)*

አብዛኛውን ጊዜ ቀንጃ ሰጪው ቤተሰብ ጥያቄው በቀረበለት ቀን ቀንጃ የሚገባ ልጁን አይሰጥም። የ“ቀንጃ ሰጡኝ” ጥያቄውን አብዛኛውን ጊዜ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ቀን ተቆርጦ ለቀንጃ ተቀባዩ ምላሽ ይሰጣል።

> *የልዡ አባት መክረን እናሳውቅሃለን ብለውኝ ከሁለት ሰንቨት [ሳምንት] በኋላ ነበር ይዤው የመጣሁ። (መላሽ$_{11}$)*

> *ማንም ሰው ቢሆን ልዡን ለሌላ ሰው ዝም ብሎ አውጥቶ አይሰጥም። ግዜ ወስዶ ተልብ [ከእራስ] ጋር መምከር ያስፈልጋል። (መላሽ$_7$)*

**(2)** ***የግምገማና የፍተሻ ጊዜ፡-*** ቀንጃ ሰጭው ቤተሰብ ልጁን ቀንጃ ወደጠየቀው ቤተሰብ ለመላክ ወይም ላለመላክ

የሚያስችለው ውሳኔ ላይ ለመድረስ የጠያቂውን ቤተሰብ የኢኮኖሚ ደረጃ፣ የቤተሰብ አባላት ብዛት፣ ቤተሰባዊ የዘር ግንድ፣ መንፈሳዊ አምልኮ፣ ማህበራዊ ግንኙነት እና የቤተሰቡ አባላት ጠቅለል ያለ ጠባይ ወይም ባህሪ ቀንጃ ጠያቂውን የሚያውቁ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃ ያሰባስባል አንዳንዴም በአካል ወደ ጠያቂው ቤተሰብ አካባቢ በመሄድ 'ስለላ' ያደርጋል። የቀንጃ ላኪው ቤተሰብ በእነዚህ መንገዶች መረጃዎችን ካሰባሰበ በኋላ ጠያቂው ቤተሰብ ቀንጃ የሚላክ ልጃቸውን በጥሩ መንገድ ሊይዘው የመቻሉ ጉዳይ እና በሚገቡት ውል መሰረት ውሌታውን የሚፈጽም ስለመሆኑ ግምገማ ያደርጋል። በግምገማው መሰረት ልጃቸውን ቀንጃ ለጠየቀው ቤተሰብ ለመላክ መወሰን ወይም አለመወሰናቸውን በመቀጠሮው ቀን ያሳውቃሉ።

*የቤተሰብን ሁኔታ ሳልጠይቅማ እንዴት ልጄን እሰጣለሁ? ቤተሰቡ ደና አደር [ሀብታም የሆነ] መሆኑን የሚያውቁ ሰዎችን ጠይቄ ነው ቀንጃ ያስገባሁት። እንዲያው በልቶ ማደሩ ብቻውን በቂ ላይሆን ይችላል። ቤተሰቡ ጤና የሚያድር ታልሆነ የኔም ልጅ ታሞ ሊመጣ ይችላል … ተቤተሰቡ ሁላ አንዱ ዛርና ቡዳ ታለበት ብየ ይሄንም አጣርቻለሁ። (መላሽ$_{7}$)*

*መጀመሪያ ልውሰደው ብሎ የመጣው ሰው ተዚያ በፊት የሌላ ሰው ላብ በልቷል [ሥራ አሰርቶ ያሰራበትን ዋጋ ለሰሪው ሳይከፍል ሲቀር] ሲባል ስሰማ ልጄን ለዚያ ሰው አልከውም ብየ ነበር። ይሄ አሁን የላኩባቸው ሰዎች ግን ለልጁም አለኝታ መሆን ይችላሉ ብየ ነው ያስገባሁት። አሁን ያለባቸው ሰዎች የግዚሃር ሰዎች ናቸው። በአካባቢው የተከበሩ የታፈሩ ሰዎች ናቸው። ነገሩን ማወቅ አለብኝ በማለት አንድ እሁድ ቀን ሰዎች [ጠያቂው ቤተሰብ] ወዳሉበት ደብር (ቤተክርስቲያን) ሀጂ የደብሩን መዋጮ ሲያስተባብሩ አየኋቸው። የሰውየው ልጆችም የመንግስት ሥራ ይዘው አዲስ አባ ነው እሚኖሩት። (መላሽ$_{3}$)*

*አሁን ግን ይችን ግንቦትን ይጨርስ ብየ ነው'ንጂ ላመጣው አስቢያለሁ። … ሚስትዮይቱ ያ'ምናምን [ኤች አይቪ ኤድስ] እንዳለባት መጀመሪያ ልጁን ስልከው አላወቅሁም ነበር። ተወሬ ወሬ ስሰማ ግን እንደተያዘች ነው። የጥር ስላሴ ዝክር ጠርተውኝ ሀጂ ነበር እና ሰትዮይቱን ሳያት ይችን አህላለች [ጠቋሚ የእጅ ጣታቸውን ጫፍ ይዘው እያሳዩ ከስታለች ለማለት]። አንድ ነገር ቢሆንብኝ ብየ እየሰጋሁ ስለሆነ ላመጣው ወስኛለሁ። ቀደም ልጁ [ቀንጃው] ሳይገባ የሰዎችን ሁኔታ ስጠይቅ ደና ሰዎች ናቸው። በእርግጥ አሁንም ቢሆን በቤታቸው ሞልቶ የተረፋቸው ናቸው። (መላሽ$_{6}$)*

*ስለማልገምት ውላችን በወረቀት ባይሆንም አይገደኝም። (መላሽ$_{3}$)*

**(3)** ***ውል መያዝ፡-*** የቀንጃ ላኪው ቤተሰብ ውሳኔ ልጁን ለመላክ ከሆነ በዚያው ውሳኔው በታወቀበት ቀን ወይም በሌላ ቀን የጽሁፍ ውል ይያዛል። አብዛኛውን ጊዜ ውል ሲያዝ ቢያንስ በቀንጃ ላኪው ሁለት እና በተቀባዩ ቤተሰብ ሁለት በድምሩ አራት ሽማግሌዎች ይመረጣሉ። አንዳንዴ የሁለቱም ቤተሰቦች ወይም የአንዱ ቤተሰብ የንስሃ (የነፍስ) አባት ሽማግሌዎች እንዲሆኑ ሊደረግ ይችላል። የሚያዘው ውል አብዛኛውን ጊዜ (ሀ) ቀንጃ የሚገባው ልጅ ቀንጃ በሚገባበት ቤት የሚቆየው የጊዜ ርዝማኔ፣ (ለ) ቀንጃ የሚገባውን ልጅ አያያዝ ለምሳሌ ምግብ፣ አልባሳት፣ የሚሰራው ሥራ፣ ትምህርት እና (ሐ) ቀንጃ የሚገባው ልጅ የቆይታ ጊዜውን ሲጨርስ ቀንጃ ከሚያስገባው ቤተሰብ የሚያገኘውን የገንዘብ ወይም የእህል አበል መጠን የሚመለከቱ ይዘቶችን ያካትታል። ውሉ ተጽፎና ተፈርሞ ሲያልቅ ላኪው ቤተሰብ ልጁን ከጠያቂው ቤተሰብ ጋር ይልካል ወይም የላኪው ቤተሰብ አባወራ ልጁን ለተቀባዩ ቤተሰብ ወስዶ አስረክቦ ይመለሳል።

*… ፈቃደኝነቴን ልጁን አሁን ለወሰደው ሰው ነገርሁት። ሽማግሌ ተሱ ሁለት ተእኔ ሁለት ሰዎችን መርጠን ውል ተይዞ ተፈራረምን። በውሉ ላይ የተስማማንባቸው ነገሮች ተጠቅሰዋል። በወረቀት ውላችንን መያዙ ለሁለታችንም መተማመኛ ነው። … ሰው እንደ'ንጨት ተሰባሪ ነውና እሚመጣው አይታወቅም። ልጁ አንድ አመት ሲቆይ 1500 ብር ሊያገኝ…. [እና] አቅሙ የፈቀደውን ሰራ ሊሰራ ነው ውላችን። (መላሽ$_{4}$)*

*ወደዚህ ስመጣ ውል ይዘን ነው። ውሉ ላይ የፈረመች እናቴ ናት። ውሉን ያፈራረሙን ሽማግሎች ናቸው። እናቴ በእህል ይሻላል ብላ ነበረ እኔ ነኝ በገንዘብ እንዲሆን ያረግሁት … ምክንያቱም ገንዘብ ተሆነ ትንሽ ለእናቴ ሰጥቼ የተበቀረውን ለእኔ ለማስቀረት እንዲመቼኝ ብየ ነው። ባመት 1700 ብር ሊከፍሉኝ ነው የተስማማን። ልብስ ተኔ ነው … ድንገት ያመትባሉ [ልብስ] አሰፋ እንደሁ'ንጅ አሁንስ አለኝ። ትምርቴን ለመማር አልተስማማንም … ከርሞ ነው እንደገና እምጀምር። አሁን ወረቀቱ [ውሉ] ያለው እናቴ ዘንዳ ነው። (መላሽ$_{14}$)*

*ውላችንን በጥሁፍ ይዘናል [የእጅ ጽሁፉ ቅጅ ለናሙናነት በስዕል 1] ። በግዜ ብዛት ቢዘነጋ እንኳ ለማስታወስ ጥሩ ነው። (መላሽ$_{12}$) የጥሁፍ ውል እንይዛለን ብለናል። የተዋዋልነው ልጁ አንድ አመት ሲቆይ ሁለት አቁማዳ [መጠኑ ከኩንታል ጋር ይመሳሰላል] ስንዴ ሊያገኝ፣ ትምርቱን ሊያስተምረው ነው። ውላችን ላይ ልጁን ልብስ ማልበስ የለም ነበረ … ግን ልብስ አልብሰውታል። ሰውየው ይከዱኛል ብየ*

ሀሙስ ሚያዚያ 27 ቀን 207 ዓ.ም
2007

ወል መዋዋል

እኔ አስ[illegible]ንቴ በወይራ ቀበሌ ገበሬ መሀበር የምኖር በዚሁ ቀበሌ ነዋሪ የሆነውን የአቶ አለ[illegible]ሀን የመጀመሪያ ልጅ ቀለቡን ችየ ትምህርቱን እያሥተማርሁ በአመት አንድ ማዳበሪያ ገብስ፡ አንድ ኩንታል ማሽላ [በቆሎ] እና አንድ ማዳበሪያ ጤፍ ልሰጠው ቀንጃ አስገብቼዋለሁ። እኔም አለ[illegible]ነህ ልጄን እንደራሱ ልጅ አድርጎ እንዲያሳድግልኝ ከላይ በተጠቀሰው የህል መጠን ወድጅ ተስማማቻለሁ። ይህ ውል የጸና የሚሆነው ከሰኞ ግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ [እስከ] ሚያዝያ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ነው። ይህንን ውል ያዋዋሉ ሽማግሌዎች፡-

1ኛ መ[illegible]ለ [የምልክት ፊርማ]
2ኛ አቶ መኩ[illegible]የ [የምልክት ፊርማ]
3ኛ ፈጠ[illegible]ለ [የአሻራ ፊርማ] እና
4ኛ አቶ ላመ[illegible]ሴ ናቸው [የምልክት ፊርማ]

**ስዕል 1** የቀንጃ ውል ስምምነት (መላሽ$_{12}$) (በእጅ ከተጻፈው የተገለበጠ ቅጅ)

ቀንጃ ሰጪው ቤተሰብ፣ ቀንጃ የገባው ልጅ ወይም ቀንጃ ተቀባዩ ቤተሰብ ከመካከላቸው አንዱ ውሉን ቢያፈርስ ተበድያለሁ ያለው ክፍል ውሉን ላዋዋሉት ሽማግሌዎች ቅሬታ ወይም ወቀሳ ያቀርባል። በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት ካልተፈታ በመደበኛ ህጎች ወይም በማህበራዊ ደንቦች ሊዳኝ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ጉዳዩ ወደ ሽማግሌዎች ወይም ወደ ሌላ የዳኝነት ሥርዓቶች ሳይደርስ ቀርቶ ውል በፈረሰበትና በውል አፍራሹ መካከል ግጭት ሊነሳ ይችላል።

> *[አሁን] እድሜዬ 14 ግድም ይሆናል። ቀንጃ … ገብቼ ሁለት ዓመት ቆየሁ። በመጀመሪያው ዓመት የለፋሁበትን ስጠኝ ስለው 'ምን ታረገዋለህ እኔ ዘንድ ይሁንልህ' ሲለኝ እኔም ቢቆጠብ ይሻላል ብየ እሽ አልሁት። ሁለተኛው ዓመቴ ሲያልቅ [ቀንጃ ያስገባኝን ሰው] ልሀድ ነው የለፋሁበትን ስጠኝ ስለው ድርሻህ ነው ብሎ የሰጠኝ በውል ከተዋዋልነው በጣም ያነሰ ሆነ። በውላችን መሰረት አስተካክለህ ስጠኝ ስለው 'እና በውላችን መሰረት ድርሻህ ይሄ ነው' ሲለኝ ሁሉንም ጥየለት ወደ እናቴ ወንድም [አጎቴ] ሀድሁ። ቀንጃ ያስገባኝ ሰው የለፋሁበትን እንደከለከለኝ ስነግረው አጎቴ በጥዋት ተነስቶ ቀንጃ ያስገባኝን ሰው ወይፈን ከመስክ ቀንድሎ [አጥፍቶ] ይዞት መጣ። በዚህ የተነሳ አጎቴ እስር ቤት ገብቶ ነበር። በኋላ ግን ሁሉንም ባይሆን ብዙውን ስለሰጠኝ በሽማግሌ ተሰማማን። (መላሽ$_{18}$)*

ከላይ ከቀረቡት የቀንጃ ውል አያያዝ ሂደቶች መረዳት የሚቻለው ቀንጃ ስርዓት ባለው መንገድ ከማህበረሰቡ ማህበራዊ ግንኙነቶች ጋር ተጎዳኝቶ የሚፈጸም መሆኑን ነው። ይህም እንደግዛቸው (2012 እ.ኤ.አ) አገላለጽ ቀንጃ ልክ እንደሚሸጥ እቃ ልጆችን ወደ ገበያ ይዞ በመውጣት የሚፈጸም ተግባር አለመሆኑን መረዳት ይቻላል። በአንጻሩ ቀንጃ ሲገባ ጊዜ ተወስዶ፣ የተለያዩ አካላት (ሽማግሌዎች) ተሳትፈውበት፣ የቀንጃ ተቀባዩና ላኪው ቤተሰቦች ተገማግመውበት እንዲሁም ቀንጃ የሚገባው ህጻን ሁኔታ ታይቶ የሚፈጸም ሥርዓት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተመሳሳይ (ሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ) ቀንጃ የራሱ የሆነ የአተገባበር ሥርዓት እንዳለው እና ይህም በማህበረሰቡ የአኗኗር ዘየ እና ነባራዊ ሁኔታ ላይ 'የበቀለ' መሆኑን ጠቅሰዋል።

## ቀንጃ ገብተው የነበሩ ሰዎች ቀንጃ ገብተውበት ከነበረው ቤተሰብ ጋር ያላቸው ግንኙነት

ቀንጃ ገብተው የነበሩ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት የግላቸውን ቤተሰብ መስርተው የሚኖሩ ግለሰቦች ቀንጃ በነበሩ ሰዓት ቀንጃ አስገብተዋቸው ከነበሩ ቤተሰቦች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት ወደኋላ እንዲያስታውሱ በማድረግ እና ከዚህ ጋር በተያያዘ ስለሚያውቁት ጉዳይ እንዲናገሩ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር። እነዚህ ተሳታፊዎች ሲገልጹ፡-

> *ብዙ ዘመዳም ሁነው የቀሩ ሰዎች [ቀንጃ ያስገቡና የገቡ] አሉ። ክርስትና የተናሱ ቢጋብቻ የተሳሰሩም አውቃለሁ። (መላሽ$_{6}$)*
>
> *ቀንጃ የገባውና ያስገቡት ሲመጣጠኑማ … ተሲጋ ዘመድ በላይ ዝምድና ይመሰርታሉ። (መላሽ$_{2}$)*
>
> *ያሁናን ባለቤቴ ያገባኋት ቀንጃ ካስገቡኝ ሰወች ነው። መጀመሪያ እዚያው ተከርቻም[ii] ሁኝ ቆየሁ። በኋላ ግን ራሳችንን ችለን ጎጆ ቀልስን መኖር ጀምረናል። የሷ ቤተሰቦች አሁንም ቢሆን ከባለቤቴ ባላይ እኔን ነው እሚወዱ። [ስለዚህ] ቀንጃ ለኔ ምሽት አስገኝቶኛል … ሳቅ …። (መላሽ$_{19}$)*

ከላይ በቀረቡት አገላለጾች መሰረት አንዳንድ ቤተሰቦች ቀንጃ አስገብተውት የነበረው ልጅ የግሉን ቤተሰብ መሰርቶ መኖር ሲጀምር በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ በተለመዱ ስርዓቶች (ለምሳሌ፡- ክርስትና በመነሳሳት፣ በጋብቻ) ቤተሰባዊ ግንኙነታቸውን እንደሚያጠናክሩ መረዳት ይቻላል። ሌላኛው መላሽ ሲገልጹ ደግሞ፡-

*ቀንጃው ተሰመረ'ማ ግንኙነቱ እስተቤተሰብ ይዘልቃል። በወንዱም በሴቱም ስራ ይተጋገዛሉ። በወንዱ ስራ... በጤፍ በራይ [እና] በአጨዳ ይረዳዳሉ፣ ወንፈል ይወናፈላሉ። በሴቱም ስራ አውጫጭኝ [ግብዣ ወይም ተዝካር] ሲኖር ይተጋገዛሉ። (መላሽ$_{1}$)*

በዚህም መሰረት አንዳንድ ቤተሰቦች ቀንጃ አስገብተውት ከነበረው ልጅ ቤተሰብ ጋር በእለት ከእለት በሚኖሩ የእርሻ ስራዎች ማለትም በአረም፣ በበራይ፣ በአጨዳ፣ በውቂያ ... ወዘተ በግል አልያም ደቦ እና/ወይም ወንፈል በመግባት እንደሚረዳዱ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ የሰርግ፣ የማህበርና የተዝካር ዝግጅቶች ከሁለቱ በአንዱ ቤተሰብ ሲኖር ሰራዎችን እንደሚረዳዱ ከዚህ በላይ ከቀረበው መላሽ ማረዳት ይቻላል።

በተጨማሪም ቀንጃ ገብተው የነበሩ ልጆች ገብተውበት ለነበረው ቤተሰብ ከሌሎች የአካባቢው ሰዎች በተሻላ አመኔታ ስለሚያሳድሩ ገብተውበት የነበረውን ቤተሰብ የእርሻ መሬት እንዲያዘምሩት በኪራይ ወይም በጥማድ እንደሚሰጧቸው ከዚህ ቀጥሎ በቀረበው መላሽ ተገልጿል።

*አሁን ተጠምጄ የማርሰው መሬት ቀንጃ አስገብተውኝ የነበሩት ሰዎች ነው። የመሬቱን ጠባይ ከቀደምም ቀንጃ ገብቼ ሳለሁ ሰለማውቀው አያስቸግረኝም። (መላሽ$_{18}$)*

ስለሆነም የቀንጃ ግንኙነት ህጻናት በአዋቂነት እድሜያቸው ጭምር ሊቀጥል የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን ከዚህ በላይ በቀረቡት የመላሽ ሃሳቦችና ማብራሪያዎች ማወቅ ይቻላል።

### *መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንጃን አስመልክቶ የሚያከናውኗቸው ተግባራት*

መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች ከህጻናት ቀንጃ ጋር በተያያዘ ያላቸውን እይታ እና የሚያከናውኗቸውን ተግባራት በተመለከት ከምስራቅ ጎጃም ዞን የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች መምሪያ ተወካይ እና አንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጀት[iv] ተወካዮች ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር።

ከዞን የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች መምሪያ ተወካይ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ቀንጃ በአስከፊ የህጻናት የጉልበት ብዝበዛ (child labor) ስር ሊጠቃለል እንደሚችል አስረድተዋል። በተጨማሪም መምሪያው ከዞን እስከ ቀበሌ (ጎጥ) ድረስ ባለው መደበኛ የመንግስት መዋቅሮቹ እና በፈጠረው ግብረ ሃይል (task force) አስከፊ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛን (ቀንጃን ጨምሮ ማለት ነው) ለመከላከልና ለማስቆም የተለያዩ ተግባራትን ለማከናወን በአመታዊ የፊሲካል እቅዱ ላይ አካትቷል። ከእነዚህ ተግባራት መካከል 'የህጻናት ዝውውርን መግታት' የሚል የሚገኝበት ሲሆን ከህጻናት ቀንጃ ጋር በይበልጥ ሊገናኝ ይችላል በማለት ተጨማሪ ማብራሪያ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቦበታል።

***ህገወጥ የልጆች ዝውውርን መግታት፡-*** መምሪያው 'ያለፍላጎታቸው' ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ህጻናት ለአስከፊ የጉልበት ብዝበዛ ተጋላጭ ናቸው በማለት ድርጊቱ እንዳይፈጸም የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ከተወካዩ ጋር በነበረው ቃለ መጠይቅ ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም የህጻናት ዝውውርን በሚፈጽሙ ግለሰቦች ላይ የህግ ቅጣት እንደሚጣልም በአስተባባሪው ተያይዞ ተብራርቷል።

*ጠያቂ፡- የልጆች ዝውውር ከጉልበት ብዝበዛ ጋር የሚገናኘው በምን መልኩ ነው?*

*መላሽ$_{20}$፡- ህገወጥ የህጻናት ዝውውር ስንል ... ያለፍላጎታቸው ከእናት አባታቸው ተለይተው ወደ ሌላ ቦታ ለስራ የሚሄዱትን ማለታችን ነው። ...*

*ጠያቂ፡- በፍላጎታቸው ወይም ያለፍላጎታቸው መንቀሳቀሳቸውን እንዴት ታውቁታላችሁ?*

*መላሽ$_{20}$፡- እርግጥ ነው የእያንዳንዱን ህጻናት[ህጻን] ፍላጎት የምናውቅበት ዘዴ የለንም ... ግን ከትምህርት ቤት አቋርጠው ከሄዱ፣ የሚሄዱት ለስራ ከሆነ፣ የሚሄዱት በገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ከሆነ ህገወጥ ነው ማለት ነው።*

*ጠያቂ፡- ... እና እንዴት ነው ከጉልበት ብዝበዛ ጋር የሚያያዘው?*

*መላሽ$_{20}$፡- በሄዱበት ቦታ ... ከአቅማቸው በላይ ሰለሚያሰሯቸው [ለልጆች] ጎጂ ያደርገዋል።... ትምህርት አይከታተሉም፣ ምግብ አይበሉም።*

*ጠያቂ፡- እነማናቸው የሚያንቀሳቅሷቸው?*

*መላሽ$_{20}$፡- እንደዞን በዚህ ተግባር ላይ የተሰማሩ ደላሎች እንዳሉ ታውቋል። ... ግን ብዙ ጊዜ በዘመዳ'ዝማድ የሚደረጉ ዝውውሮች ይበዛሉ ብየ እገምታለሁ። ህጻናትን በማዘዋወር ላይ የተሰማራ አንድ ደላላ በህግ እንዲጠየቅ አድርገናል።*

*ጠያቂ፡- በዘመድ አዝማድ አማካኝነት በሚደረጉ ዝውውሮች ላይስ?*

*መላሽ$_{20}$፡- በእነሱ የሚንቀሳቀሱ ህጻናትን [በህግ] ለመጠየቅ መረጃ [ማስረጃ] አናገኝም። [ምክንያቱም] ... ተሳትፈዋል የተባሉ ሰዎችን ስንጠይቅ 'እኔ አይደለሁም እንዲሄድ ያደረግሁ፣ ልጁ በራሱ ፍላጎት ነው' ይላሉ። ... እና ብዙ ጊዜ [እርስ በእርሳቸው] ይሸፋፈናሉ።*

የቀንጃ ሥርዓት ከህገወጥ የህጻናት ዝውውር ጋር እንደሚያያዝ እና ድርጊቱ የህጻናትን መብት እንደሚጋፋ የሁለቱ ድርጅት ተዋካዮች ገልጸዋል። የዞን መምሪያው ተወካይ ስለቀንጃ ያላቸውን እይታ እና የሚያከናውኛቸውን ተግባራት አስመልክቶ ሲመልሱ፡-

*ጠያቂ፡- በገጠሩ ማህበረሰብ አካባቢ የልጆች ቀንጃ የሚባል 'ልማድ' አለ። ከህገወጥ የልጆች ዝውውር ጋር ይገናኝ ይሆን?*

*መላሽ$_{20}$፡- ... በአንዳ'ንድ አካባቢዎች ቀንጃ መስደድ አማራጭ የገንዘብ ማግኛ ተደርጎ እየተከናነ ነው...። እንዲያውም የዞን መመሪያው ... [ከአጋር አካላት] ጋር በመሆን ህጻናትን ቀንጃ መላክ ጎጂ ትራዲሽናል ፐራክቲስ [ልማዳዊ ድርጊት] ነው ... [ተብሎ ድርጊቱን ለማስቀረት] የተለያዩ ተግባራትን እያከናወን ነው።*

*ጠያቂ፡- ምን ምን ተግባራትን እያከናወናችሁ ነው?*

*መላሽ$_{20}$፡- አንደኛ እሁድ እሁድ [በቤተክርስቲያን] በአውደ ምህረት ላይ ቀንጃ የላኩ ሰዎችን ስማቸው እየተጠራ እንዲወቀሱ እናደርጋለን፣ [ሁለተኛ] … በኮንፈረንሶች ላይ የአዌርነስ ክሬሽን [የግንዛቤ ማስጨበጫ] ስራ እንሰራለን፣ [ሶስተኛ] … በድህነት ምክንያት ቀንጃ ለገቡ ህጻናት ቤተሰቦች የገቢ ማግኛ አማራጮች እንደ ዶሮ ማርቢያ ያሉ ስራዎችን እንዲሰሩ የማቴሪያል [የቁሳቁስ] ና የትሬኒንግ [የስልጠና] ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል።*

*ጠያቂ፡- ስለዚህ ቀንጃ መላክ አሁን እየቀነሰ ነው ማለት ይቻላል?*

*መላሽ$_{20}$፡- ተደብቀው የሚልኩ [ወላጆች] አንዳንድ ጊዜ አሉ። … [ግን] በተሰራው ሥራ ብዙ ልጆች ቀንጃ እንዳይሄዱ አድርገናል …። ስንጠይቃቸው ቅድም ያልሁህን አይነት ምላሽ [‘እኔ አይደለሁም እንዲሄድ ያደረግሁ፣ ልጁ በራሱ ፍላጎት ነው’] ነው የሚያቀርቡልን።*

*ጠያቂ፡- እንደዚህ በሚያደርጉ ወላጆች ላይ እየተወሰደ ያለ እርምጃ አለ?*

*መላሽ$_{20}$፡- እስካሁን ብዙ እያተሰራበት ያለው በአዌርነስ ክሬሽን [የግንዛቤ ማስጨበጫ] ላይ ነው። … በተደጋጋሚ ልጃቸውን በላኩ በተወሰኑ እናትና አባቶች ላይ በእድር እና በማህበራዊ ፍርድ ቤት እንዲጠየቁ የማረግ ስራ እየተሰራ … ነው…።*

*ጠያቂ፡- ምን አይነት እርምጃ ተወሰደባቸው?*

*መላሽ$_{20}$፡- እንደዚህ ያረጉ ሰዎች’ማ [ልጃቸውን በተደጋጋሚ የላኩ] ከእድር እስከማሳገድ እና እስር ቤት እንዲገቡ እስከማረግ ሊቀጡ ይችላሉ።*

*ጠያቂ፡- ለመሆኑ ልጆችን ቀንጃ መላክ ጎጂ እንዲሆን ያደረገው ምንድን ነው?*

*መላሽ$_{20}$፡- [ልጆች] ቀንጃ ሲላኩ በግዳጅ መሆኑ፣ ትምህርታቸውን እንዲያቋርጡ መደረጉ … ነው ጉዳዩን የከፋ የሚያደርገው።*

በተመሳሳይም መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት ተወካዩ ቀንጃን አስመልክቶ ያላቸውን አስተያየትና ድርጅታቸው የሚያከናውናቸውን ተግባራት በሚከተለው ቃለ ምልልስ አብራርተዋል።

*በዚህ ዞን የገጠሩ አካባቢ ለብዙ ህጻናት ደህንነት እንደትሬት [ስጋት] ሁኖ ያለው ጉዳይ ቀንጃ ነው። በለጋ እድሜቸው ወደ ቀንጃ ይላካሉ። ተልከው ከአቅማቸው በላይ ሰራ በተላኩበት ቤት ይሰራሉ። በሌሊት ቅራት ይቀራሉ በቀን የእርሻ ሥራ ይሰራሉ። (መላሽ$_{21}$)*

ልጆችን ቀንጃ ሲላኩ ምግብና ልብስ በአግባቡ እንደማያገኙ እና ከትምህርት ገበታቸው እንደሚያቋርቱ ወይም ደግሞ ትምህርት ቤት ሳይገቡ እንደሚቀሩ የዚህ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ተወካይ በቃለ ምልልሱ ወቅት ገልጸዋል።

*… እነዚህን ሁላ ስራዎች የሚሰሩ ምግብ በቀን ሶስቴ እንኳ ሳይበሉ ነው። የሚለብሱት ልብስ ሳይኖራቸው ነው። ወደ ቀንጃ ሲላኩ ከትምህርት ቤት አቋርጠው ነው። አንዳንድ ግዜ ደ’ም ገና ወደ ትምህርት ቤት ሳይገቡ ነው። ትምህርት ሳይማሩ እድሚያቸው እንዲሁ በከንቱ ነው የሚያልፍ። (መላሽ$_{21}$)*

በተጨማሪም በዞኑ በሁሉም ወረዳዎች ልጆች ቀንጃ እንዳይላኩ ለመከላከል ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በማውጣጣት የህጻናት ጥበቃ ምክር ቤት መቋቋሙን ተወካዩ እንደሚከተለው ገልጸዋል።

*የተለያዩ አካላትን በማቀናጀት የህጻናት ጥበቃ ምክር ቤት አለን። ከሴቶች ጉዳይ፣ ከፖሊስ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከእድር እና ከአካባቢ ሽማግሌዎች በ16ቱም ወረዳዎች አለን። በዚህ ምክር ቤት ማ’ነው ልጁን ከትምህርት ቤት ያስቀረ፣ ማ’ነው ልጁን የዳረ፣ ማ’ነው ልጁን ቀንጃ የላከ የሚሉ ጉዳዮችን ያያል። (መላሽ$_{21}$)*

በመጨረሻም ቀንጃ እንዳይገቡ የተደረጉ ልጆችን ብዛት በቁጥር መግለጽ ባይችሉም ብዙ ልጆችን ከቀንጃነት ህይወት እንደተከላከሉ እንዲሁም ቀንጃ የሚያስገቡ ወላጆች ልጃቸውን ቀንጃ በመላካቸው ምክንያት በህግ ሊያስቀጣ እንደሚችል የድርጅቱ ተወካይ በሚከተለው ምልልስ አስረድተዋል።

*ከባለፈው አመት ጀምሮ ብዙ ህጻናትን ከቀንጃ አስቀርተናል። … በቁጥር ይሄነው ብየ ባልነግርህም ብዙ ህጻናት ናቸው። … ወደ ህግ ድሮስ ሊወሰዱ ይችላሉ። እድሜው ለሥራ ያልደረሰን ልጅ ቀንጃ መላከ ወንጀል ነው። የሰራተኛ አዋጁን እንኳ ብታየው ከ18 ዓመት በታች የሆነውን ህጻን ማታ ማሰራት ክልክል እንደሆነ አስቀምጧል። እና ስለዚህ ያስቀጣል። (መላሽ$_{21}$)*

### ***ቀንጃ የገቡ ልጆች በቀንጃ ቤት የሚያጋጥማቸው ሁኔታ***

#### ***ሀ) የሚያከናውኗቸው ተግባራት***


ቀንጃ ልጆች ከሰኞ እስከ እሁድ ባሉት ቀናት ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን ሊሰሩ ይችላሉ። እንደአመችነታቸው አንዳንድ ተግባራትን ጎን ለጎን ወይም በጣምራ አንዳንዶችን ደግሞ ለብቻቸው ሊያከናውኗቸው እንደሚችሉ ቀንጃ የገቡ ልጆች በቃለ ምልልሱ ወቅት ጠቅሰዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ቀንጃ ከገቡ ልጆች መካከል የአንዱ ሃሳብ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል።

*ከብት እየጠበቅሁ ብዙ ስራዎችን አብሬ [ጎን ለጎን] እሰራለሁ። [ከብት እየጠብቅሁ] እጫወታለሁ፣ ጅራፍ እፈትላለሁ፣ እንጨት እለቅማለሁ፣ አጠናለሁ። (መላሽ13)*

ቀንጃ ህጻናት በፈረቃ ትምህርት ቤት ግማሽ ቀን ተምረው ሲመለሱ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን የእለት ውሏቸውን እንደሚያሳልፉ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ቀንጃ ህጻናት ጠቅሰዋል። ትምህርት ቤት ከገቡ ቀንጃ ልጆች መካከል የ14 ዓመት እና የስድስተኛ ክፍል ተማሪ የሆነውን ቀንጃ ቃለ መጠይቅ ከተደረገበት ቀደም ብሎ ባለው ቀን ያከናወናቸውን ዋና ዋና ተግባራት ለዚህ ተብሎ የተዘጋጀውን በግል የሚሞላ የውሎ ቅጽ እንዲሞላ ተደርጓል። የተሞላው ቅጽ (በስዕል 2) እንደሚያሳየው ይህ ልጅ በቀን ውስጥ በርካታ ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን እነዚህን ተግባራት ይበልጥ ለመረዳት እንዲቻል ተግባራቱ የሚከናወኑበትን ሰዓት መሰረት በማድረግ እና በምድብ በመከፋፈል በስዕል 3 ቀርቧል።

| | ሰዓት | የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት |
|---|---|---|
| ቀን | ከሰዓት በፊት (ጥዋት) | ፊት መታጠብ፣ ከብት መደነብ፣ በሬ ማብላት፣ ውተት ማለብ፣ የበሬ እቃ ማዘጋጀት፣ ልብስ ማስቀመጥ፣ ቁርስ መብላት፣ የከብት ቤት መጥረግ፣ ጭድ መሸከም፣ በሬ ውሃ ማጠጣት፣ ምሳ ማድረስ፣ ምሳ መብላት፣ መተጣጠብ፣ ልብስ መቀየር፣ ለትምህርት ቤት፣ ጨዋታ |
| | ከሰዓት በኋላ | ትምህርት መማር፣ ጨዋታ፣ ጥጃ ፍለጋ፣ ከብት ማለብ፣ የበሬ እቃ ማምጣት |
| ማታ | ከመኘታ በፊት | በሬ ማብላት፣ ከብት ማስገባት፣ እግር መታጠብ፣ ጨዋታ፣ እራት መብላት |
| | መኘታ | እንቅልፍ |

*ስዕል 2 የውሎ ተግባራት (መላሽ$_{14}$)*




*ስዕል 3 የውሎ ተግባራት (መላሽ$_{14}$)*

በተመሳሳይም ቀንጃ የገቡ ህጻናት የተለያዩ ስራዎችን እንደሚሰሩ ሶፍያና ታጠቅ (2016 እ.ኤ.አ) በጥናታቸው ጠቅሰዋል። ሆኖም ግን በአብዛኛው የገጠር አካባቢ የሚኖሩ ህጻናት (ቀንጃ ያልገቡትም ጭምር) በርካታ ስራዎችን እንደመስራታቸው (አሰፋና በዲ፣ 2003፤ ጌትነትና በልዩ፣ 2012; አርኪን፣ 2012፤ ታጠቅ፣ 2010 እ.ኤ.አ) እንዲሁም ልጆችን በስራ የማሳተፍ ተግባር በመደበኛው የልጆች አስተዳደግ ሥርዓት ውስጥ እንደመገኘቱ (አብርሃም፣ 1996) እና ቀንጃ ከልጆች አስተዳደግ ዘየ ጋር የተገናኘ እንደመሆኑ (ሶፍያና ታጠቅ፣ 2016 እ.ኤ.አ) መጠን እነዚህ ቀንጃ በገቡ ህጻናት የሚያከናወኗቸው ተግባራት ቀንጃ በመግባታቸው ምክንያት ላይሆን የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል። ይህም ማለት ቀንጃ የገቡ ህጻናት ልክ በገጠር እንደሚኖሩ እንደአብዛኛው ህጻናት የሚሰሯቸው ተግባራት ሊሆኑ ይችላሉ።

ቀንጃ የገቡ ህጻናት በቀን ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እንዲዘረዝሩ ከማድረግ በተጨማሪ የሚወዷቸውንና የሚጠሏቸውን ስራዎች እንዲጠቁሙ ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር። በዚህም መሰረት ከብት ወይም በግ መጠበቅ የትምህርት ቤት የቤት ስራ ለመስራት፣ ጥናት ለማጥናት፣ ለብቻ ወይም ከጓደኛ ጋር ለመጫወትና ስለተለያዩ ጉዳዮች ለመወያየት የሚያመች በመሆኑ እና በአንጻራዊ ከአዋቂዎች እይታ የራቀ ስለሆነ ለቀንጃ ልጆች የነጻነት ስሜት ስለሚያሳድርባቸው ከሌሎች ስራዎች ተመራጭነት እንዳለው እነዚህ ህጻናት ጠቅሰዋል። እንዲሁም ተልኮ መልእክት ወይም እቃ ለማድረስ ወደ ሌላ ሰው ወይም ቤት ሲሄዱ አንጻራዊ ነጻነት ስለሚያገኙ መላክን እንደሚወዱ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሃሳቦች ያስረዳሉ።

> *… ተሰራዎች ሁሉ ብሰራ ደስ እሚለኝ ከብት መጠበቅ ነው። [ምክንያቱም] ለመጫወትና ተሌሎች ልዦች ጋር ለመገናኘት ስለሚያመች። ስንገናኝ ትረት ትረት እንጫወታለን። (መላሽ$_{13}$)*

> *ከብት እና በግ ስጠብቅ ጥናት አጠናለሁ፣ የቤት ስራየንም እሰራለሁ። ደብተሬንና መጽሃፌን በጀርባየ ሻጥ አርጌ ወደ ሜዳ ተከብቶች ጋር እሁዳለሁ። ሳር ታገኙ ከብቶች አያስቸግሩኝም። ጥላ ስር እምበለበልና አጠናለሁ። [ስለዚህ] ሁልግዜ ከብትና በግ ብጠብቅ ደስ ይለኛል። (ምላሽ$_{14}$)*

> *ታንዳንድ ቀን ተልኬ ኢቃ አድርስ ስባል ደስ ይለኛል። … በመንገድ ጉብላሊቱን [ልጆችን] ታገኝሁት እጫወታለሁ። (ምላሽ$_{16}$)*

በአንጻሩ ቀንጃ አስገቢዎች ቀንጃ ልጆች ጨዋታ እንዲጫወቱ እንደማይፈቅዱላቸው እንዲሁም ከአካባቢያቸው

እንዲርቁም እንደማይፈልጉ ቀንጃ የገቡ ልጆች ከዚህ በታች በቀረቡት ሃሳቦች ጠቁመዋል።

*ተልኬ ስሃድ ቶሎ ተመለስ እባላለሁ። ስሀድ በመንገድ እንዳልቆም ያስጠነቅቁኛል። (መላሽ$_{16}$)*

*ቀን ተረት ተረት መጫወት አጎት ይገድላል ብለው ተረት እንዳልጫወት ያስፈራሩኛል። እኔ ግን ዝም ብየ እጫወታለሁ። አጎቴ ግን አልሞተም። አውቀው ይመስለኛል። (መላሽ$_{17}$)*

በሌላ በኩል ደግሞ አንጻራዊ እረፍት የማይሰጡ እና ከአዋቂዎች ጋር ሁነው የሚሰሩ ሥራዎች (ለምሳሌ፡- አረም ማረም፣ በራይ፣ እርሻ) ቀንጃ በገቡ ልጆች ዘንድ ተወዳጅነት እንደሌላቸው ቀንጃ የገቡ ልጆች ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት የቃለ መጠይቅ ምላሾች ተናግረዋል።

*አረም ሳርም ተዋልሁ ወገቤ ቁርጥ ይላል፣ ከንዴንና ትክሻየን ያመኛል። ቀን ሙሉ ነው ስናርም እምንውል። በክረምቱ የጤፍ የጭቃ በራይ ስውልም ደከሞኝ ነው እምውል። አረም ና በራይ ውየ ማታ ስተኛ የወደቅሁበትን ሳልሰማው ነው ማልዳ እምነቃ። (ምላሽ$_{13}$)*

*ሰውየው ባገር ተሌለ እኔ ነኝ ቆቻ [ቀኑን ሙሉ ሲያርሱ መዋል] እምውል። ረፍት የለውም … ምሳ ሰበላ እንኳ በሬዎችን እንደጠመድሁ ነው። (ምላሽ$_{15}$)*

## *ለ) ቀንጃ እንደገቡ የሚያጋጥማቸው*

ከአካባቢያቸው ራቅ ብለው አዲስ ቀንጃ የገቡ ልጆች መደናገጥና ፍርሃት ስሜት እንደሚሰማቸው ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የቃለ መጠይቅ ምላሾች ያሳያሉ። ቀሰ በቀስ ቀንጃ የገቡበትን አካባቢ እየለመዱት ሲመጡ የባይተዋርነት ስሜቱ እንደሚቀንስላቸው መላሾች አያይዘው ጠቁመዋል።

*መጀመሪያ'ማ እምለምድም አልመስሎኝ ነበር። አሁን ግን ለምጃለሁ። ጓደኞች አሉኝ። ከብት ስንጠብቅ እንገናኛለን። (ምላሽ$_{17}$)*

*ወደዚህ ስመጣ ለግዜው ግር ብሎኝ ነበር። እዚህ ተራራና ወንዝ ይበዛል። እኛ አገር ግን ሜዳ ነው። ወንዝም አንድ ብቻ ነው ያለው። አሁን ተለማምጃለሁ። (ምላሽ$_{14}$)*

*በመጣ እስተሳልስት [እስከሶስት ቀን] ድረስ ጎጃም አዘነውን [ፎጣውን] ተከናንቦ ነበር እሚውል። ትንሽ ቀን ተቆየ በኋላ ግን አየሩን ተለማምዶታል። (ምላሽ$_{11}$)*

ከዚህ በተጨማሪ ቀንጃ የገቡ ልጆች በቀንጃ ተቀባይ ቤተሰቦች ባሉበት ጊዜ ከሚጠብቋቸው ከብቶች፣ ፍየሎች ወይም በጎች አንዱ ቢጠፋባቸው የጠፋውን እንሳሳ እንደሚከፍሉ ማስጠንቀቂያ ሊነገራቸው ይችላል። ሆኖም ግን ይህ ማስጠንቀቂያ ቀንጃ ህጻናት ሥራቸውን በጥንቃቄ እንዲሰሩ ለማድረግ ሲባል ብቻ እንደሆነ እና ቀንጃ የገባው ልጅ ከሚጠብቃቸው እንስሳት መካከል ቢጠፋበት በእርግጥ ለማስከፈል ወይም ከፍሎ የሚያውቅ ቀንጃ እንደሌለ ቀንጃ ተቀባዮች ገልጸዋል።

*ኢያ [ስም ጠቅሶ] ከብት ካጠፋህ ከአበልህ ላይ ነው እምቆርጠው ይለኛል። እኔ ግን መጀመሪያም እንዳይጠፉብኝ አርጌ ነው ከብት እምጠብቅ። … አይበለውና ቢጠፉብኝ ግን እሚቆርጥብኝ አይመስለኝም። (መላሽ$_{15}$)*

*አንድ ደካማ ላም አንድ ቀን በጉርጓድ ገብታ ጠፍታ ነበር። ላሚቱ ጠፍታ ያደረች እለት ማታ ሴትዮይቱ [እማወራዋ] 'ያች ላም ትጥፋና ከአበልህ ላይ ነው እምንቆርጠው' አለችኝ። ላሚቱ ጠዋት ስትገኝ ደስ አለኝ። (መላሽ$_{17}$)*

*… [እንቆርጥብሀለን] ለማለትማ እንላለን። ግን አይቆረጥበትም እስታአሁን በአካባቢያችን ሲቆረጥ አይቼ አለውቅም። ይቆረጥብሀል እምንለው ተግቶ እንዲሰራ ጨዋታ እንዳያበዛ በሚል ነው። (መላሽ$_{8}$)።*

ቀንጃ የገባው ልጅ በሥራው ላይ መዘናጋት ካሳየ ቀንጃ ተቀባዮች ለላኪ ወላጆቹ እንዲነገር ሊደረግ እንደሚችል የጥናቱ ተሳታፊዎች ገልጸዋል። ቀንጃ የገባው ልጅ የስነ ምግባር ግድፈቶችን (ውሸት፣ ሌብነት፣ … ወዘተ) በተደጋጋሚ ካሳየ ቀንጃ ተቀባዩ ቤተሰብ ልጁን ከትኩረት መንሳት እስከ አካላዊ ድብዳባ ሊደረስ የሚችል የቅጣት አይነት ሊቀጣው እንደሚችል ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት መላሾች ጠቁመዋል።

*የታዘዘውን ስራ ትቶ ሲያፉድስ [ሲጫወት] ተዋለ ለኔ ምን ይጠቅመኛል። እመከረውና ለማስተካከል እሞክራለሁ። … ድብድባማ እንዴት አረገዋለሁ የሰው ልጅ አይደል [የስጋ ልጄ አይደለም]። ለአባቱ መልክት እልካለሁ አባቱ ነግሮት የማይሰተካከል ተሆን የለፋበትን ሰጥቼ እሰደዋለሁ። (መላሽ$_{10}$)*

*ቀጠፊ [ውሸታም] ና ወስላታ [ሌባ] እንዳይሆን ሁልግዜ እመክረዋለሁ። … እንዲያውም አንድቀን የሆነ ነገር ቀጥፎኝ በለበጥ ቂጡን ሾጥ አድርጌው ተዚያች በኋላ ሳይደግማት በዚያችው እርግፍ አርጎ ተዋት። (መላሽ$_{12}$)*

*… ተግንባራቸው ነው እማውቀው። አንዳንድ ቀን ከብቶች ሆዳቸው ሳይጠግብ ወደ ቤት ማታ ማታ ተመጡ ሰውየው ግንባሩን ያኮሳትርብኛል … እኔም ጥፋቴን ስለማውቀው ዝም እላለሁ። ጥጃዎች አምልጠውኝ ተተራከቡ [ወተት ሳትታለብ ላም ከጥጃዋ ጋር ስትገናኝ] ሴትየዋም ግንባሯ ታኮሳተርብኛል። (መላሽ$_{16}$)*

## *ሐ) ምግብና አልባሳት*

ብዙዎቹ ቀንጃ የገቡ ልጆች በአብዛኛው ቀን ሶስት ጊዜ (ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት) ምግብ እንደሚያገኙ ጠቅሰዋል። በቤት ውስጥ ካሉ እኩዮች በጋራ በአንድ ማእድ የሚመገቡ ቀንጃ ህጻናት እንዳሉ ሁሉ ለብቻቸው ተለይቶ ምግብ የሚሰጣቸውም መኖራቸውን በቃለ ምልልሱ ወቅት ገልጸዋል።

*ጥሩ ነው አሁን እንደልቤ ነው እምበላ። እቤት ታሉ ልጆች ጋር አብረን እንበላለን። አንዳንድ ቀን ሁላችንም በሰርቪስ ለየብቻችን እንበላለን። (ምላሽ$_{14}$)*

*እቤቴ እያለሁ ታሁን ታሁን [ምግቡ] አለቀ እያልሁ አስብ ነበር። አሁን ግን ያለ አሳብ ያገኘሁትን እበላለሁ።… ደና ነው። እንደነሱ*

*እሆናለሁ። እነሱ ተበሉ እኔም እበላለሁ … ታልበሉ እኔም አልበላም። … እና እነሱ ታልበሉ እኔ ልበላ ኑሯል? (መላሽ$_{13}$)*

*ሁልግዜ ብቻየን ነው እሚሰጠኝ። የሰትየዋ ልጆች ተኔ ጋራ አይበሉም። ብቻቸውን ነው እሚሰጣቸው። ግን ብላት [ፍስክ] ተሆነ ቁርስ፣ ምሳ እራት እበላለሁ። (ምላሽ$_{15}$)*

በተቃራኒው ቀንጃ የገቡ ልጆች በቀንጃ ተቀባዩ ቤተሰብ ውስጥ ያለው አመጋገብ ከእነሱ ቤተሰብ ከነበረው እንደማይሻል የተናገሩም አሉ።

*እምበላው እቤቴም አላጣሁም ነበር። እንዲያውም እዚያ ሳይሻል አይቀርም። ግን እዚህ የግሌን ወረት [መነሻ ካፒታል] እያጠራቀምሁ ነው ያለሁት። (መላሽ$_{16}$)*

ነገር ግን በአንዳንድ ቀንጃ ባስገቡ ቤተሰቦች ውስጥ ለቅንጃዎች የሚሰጠው ምግብ ከቤተሰቡ የተለየ ወይም በጥራትና በመጠን ያነሰ ምግብ እንደሆነ ቀንጃዎች ያስረዳሉ።

*ሰትየዋ ክፉ ናት። አንዳንድ ቀን ደረቅ እንጀራ ብቻ በልቼ አድራለሁ። ድንች በተቀቀለ ቀን ድንች ላጥ ተብየ ስልጥ ቆይቼ የላጥሁትን ለእነሱ ሰጠቼ ለኔ ታልተላጠው ይሰጡኝና በአዋዜ እበላለሁ። … አሁን ባለፈው ክረምት ብዙ ጎመን ተትንሽ እንጀራ ጋር ነበር ስበላ የነበር። (መላሽ$_{17}$)*

*አንዳንዱ ቤት’ማ አበላል [አመጋገብ] ላይ በቤተሰቡ መካከል ልዩነቶች አለ። መጀመሪያ ቀንጃ ገብቼበት በነበረው ቤት እነሱ በወጥ እንጀራ ተበሉ ለእኔ በበርበሬ እንጀራ ይሰጡኝ ነበር። እንዲያውም ቀንጃዎች ስራ ሲሰሩ … ‘ዝናቡ ዘነበ ሰኔ አቆለቆለ በግማሽ እንጀራ ጎመን ተቆለለ’ ብለው ይዘፍናሉ። (መላሽ$_{18}$)*

ቀንጃ የገቡ ልጆች ሌሊት ለብሰውት የሚያድሩትን ልብስ ቀን በበረዳቸው ሰዓት እንደሚለብሱት ጠቅሰዋል።

*ለሊት እምለብሰው ጎጃም አዘነ [ፎጣ] አለኝ። ሟቀት ነው። ልብስ ግን አልቆብኛል … በመስረም እገዛለሁ ብያለሁ። (መላሽ$_{15}$)*

*ጎጃም አዘነውን ድሪቶ አሰፍቼው ለማታ ይሆነኛል። ታንዳንድ ቀን ብርድ ሲሆን ቀንም እለብሰዋለሁ። (መላሽ$_{16}$)*

### *መ) መደበኛ ትምህርት*

አንዳንድ ቀንጃ የገቡ ልጆች ግን በቀንጃ ውላቸው ላይ ትምህርት ማስተማር ስላልተካተተ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ እንዳልሆነ እና ትምህርቱን ባለመከታተሉ ምክንያት የደረሰበትን ሲጠቅስ የሚከተለውን ብሏል።

*ውል ስንይዝ ትምርት እምትማር ተሆነ ታበልህ እቀንሰብሃለሁ አለኝ። ትንሽ ቀን ልሰራራና በኋላ ትምርት ብቀጥል ይሻላል በየ ነበር። … ግን የልማት ቡድኖች እየመጡ ሰውየውን [ቀንጃ ያስገባውን ሰው] ትምርት ቤት ታላስገባኸው እያሉ እየጨቀጨቁት ነው። (ምላሽ$_{15}$)*

ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው አምስት ቀንጃ የገቡ ልጆች መካከል ሁለቱ ትምህርት ቤት የገቡ መሆናቸውን በቃለ ምልልሱ ወቅት ተናግረዋል። ከትምህርት ቤት መልስ ወደሥራ ስለሚሄዱ ለማጥናትና የቤት ሥራ ለመስራት የጊዜ እጥረት እንደሚያጋጥማቸው አያይዘው አብራርተዋል።

*ማታ ማታ ለማጥናት አቅዳለሁ [ግን] ማታ እንቅልፍ ይጥለኛል። አንዳንድ ቀን የቤት ሥራ ሳልሰራ ወደ ትምርት ቤት እኅዳለሁ። [የቤት ስራ ሳልሰራ ስቀር] … አስተማሪዎች ‘ተክፍል ውጣ’ ይሉኛል። (መላሽ$_{14}$)*

እነዚህ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉ ቀንጃዎች በዘር እና በውቂያ ጊዚያት አብዛኛውን ቀናት ከትምህርት ቤት እንደሚቀሩ ተናግረዋል። የትምህርት ቤት መምህራን እና የአካባቢው የመንግስት አስተዳደር ተጠሪዎች ቀንጃ ያስገቡ አባወራዎችን ከትምህርት ቤት በቀሩት ቀንጃዎች ምክንያት ቅጣት እንደሚጣልባቸው ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ምላሾች አያይዘው ጠቅሰዋል።

*በሰኔ በግንቦት እና በጥር በታህሳስ የግብርና ስራው ስለሚያፋፍመን ልዠን ከትምርት [ሳስቀረው] መምራን እየመጡ ማስጠንቀቂያ ይሰጡኛል። (መላሽ$_{9}$)*

*በጥር ጤፍ ስናበራይ [ስንወቃ] አንድ ሳምንት ከትምርት ቀርቼ ሳለኍ ሊቀመንበሩና የልማት ቡድኖች መጠው ፖሊስ ጣቢያ ይዘውት ሀደው 50 ብር ተቀጣ። … ያውም እኮ ሊቀጡት እንደሚችሉ ሰውየው ነግሮኝ ነበር። (መላሽ$_{14}$)*

እስኪርፕቶ፣ እርሳስ፣ ወረቀት ወይም ሌላ የቀንጃው መገልገያ የሆኑ ነገሮችን (ለምሳሌ ጅራፍ፣ ዱላ) በቀንጃ ተቀባዩ ቤት ውስጥ ያሉ ልጆች ከቀንጃዎች የለፈቃዳቸው ሲወስዱባቸው አልፎ አልፎ በመካከላቸው መጣላት እንደሚፈጠር ሁለት ቀንጃ የገቡ ልጆች ገልጸዋል። እነዚህ ቀንጃ ቀንጃ የገቡ ልጆች እንደዚህ አይነት ጥሎች እንዳይፈጠሩ የተለያዩ ስልቶችን እንደሚጠቀሙ በሚከተሉት ምላሾቻቸው ጠቁመዋል።

*ስራ በሀደሁበት ታኮረጆየ [ቦርሳዬ] ደብተሬን አውጥተው ያበላሹብኛል። እስክሪቢቶየንም ይወስዱብኛል። ትምርት ቤት ሀጀ ለመጣፍ ኮረጆየን ስበረብር እስክርቢቶየን አጣዋለሁ። ተጎኔ አብረውኝ ተተቀመጡት ጉብሎች [ልጆች] ለምኜ እጥፋለሁ። ተደብተሬ መሃል ሉክ [ወረቀት] ተቀዶለት አገኛለሁ። እቤት ሀጀ ማነው እስክርቢቶ የወሰደ ስላቸው አልወሰድንም ብለው ይሰድቡኛል። አሁን ግን አርፌ ያቸዋለሁ በማያገኙት ቦታ ደብቄ አስቀምጠዋለሁ። (መላሽ$_{14}$)*

*እስክሪብቶየንና ደብተሬን እየሰረቁ ሲያስቸግሩኝ ስራ ስሀድ በኮረጆየ አርጌ ይዠው ስራ እኅዳለሁ። (መላሽ$_{13}$)*

### *ህጻናት ቀንጃ በመግባት ሂደት ያላቸው ተሳትፎ*

በቀንጃ ቤት ያሉ ልጆች ቀንጃ ከመግባታቸው በፊት ቀንጃ ሊገቡ እንደሚችሉ ከላኪ ቤተሰቦቻቸው መነገራቸውን ወይም ያለመነገራቸውን እና ቀንጃ መግባታቸን ፈልገውት ነው

ወይስ ሳይፈልጉት የሚሉትን ነጥቦች ለመረደት ቀንጃ ገብተው ያሉ ህጻናት ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው ነበር። በመሆኑም ቀንጃ እንደሚገቡ ከነበራቸው መረጃ እና ለመግባት ከነበራቸው ፍላጎት አኳያ አራት አይነት ገጽታ (ስዕል 4) ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ገጽታዎች በቃለ-ምልልስ ውቅት ከተገኙ የመላሾች ሃሳብ ጋር በተጓዳኝ ከዚህ ቀጥሎ ቀርበዋል።

(1) ቀንጃ ለመግባት ፍላጎት የነበራቸውና ቀንጃ ከመግባታቸው በፊት ቀንጃ እንደሚገቡ መረጃ የነበራቸው፣
*ቀንጃ ከመምጣቴ በፊት ቀንጃ እንደምሄድ ቤተሰቦቼ ይነግሩኝ ነበር። ... [እኔም] ቀንጃ መሄዱን እፈልገው ነበር። (መላሽ16)*

(2) ቀንጃ ለመግባት ፍላጎት የነበራቸው ነገር ግን ቀንጃ እንደሚገቡ መረጃ ያልነበራቸው፣
*ቀንጃ እንደምገባ የሰማሁት አሁን ቀንጃ ያመጣኝ ሰውየ ሊጠይቅ ሲመጣ ነው። ለግዜው ትንሽ ተደናገጥሁ። እናቴ 'እንዳትሳቀቅብን ብለን ነው እስታሁን ያልነገርንህ' ብላኝ ነበር። ለግዜው ብደናገጥም ቆይቼ ግን ብጎድ እንደሚሻል ቆረጥሁ። (ምላሽ15)*

(3) ቀንጃ ለመግባት ፈላጎት ያልነበራቸው ነገር ግን ቀንጃ እንደሚገቡ መረጃ የነበራቸው፣
*ቤተሰቦቼ እንዳይቸገሩ አንድ የሆነ ስራ መስራት እንዳለብኝ አስብ ነበር። ... ቤተሰቦቼ ቀንጃ ከመግባቴ በፊት ቀንጃ መግባት እንደሚሻል ይነግሩኝ ነበር። እኔ ግን ቀንጃ መግባቱ ጥቅሙ ያን ታህል ነው ብየ ከተማ ገብቼ ብሸቅል ይሻላል ብየ ነበር። አባቴ ግን ከተማ 'ጠባይ ያበላሻል' ብሎ ወደዚህ ላከኝ። (መላሽ14)*

(4) ቀንጃ ለመግባት ፍላጎት ያልነበራቸውና ቀንጃ እንደሚገቡ መረጃ የሌላቸው ናቸው።
*[ቤተሰቦቼ] ቀንጃ መግባት እንደማልፈልግ ስለሚያውቁ ቀንጃ እንደምገባ አልነገሩኝም ነበር። ቀንጃ እንደምገባ ያወቅሁ [አሁን ያለሁበት ሰው] ቀንጃ ሊወስደኝ ሲመጣ ነው። (ምላሽ17)*

| | ***ቀንጃ እንደሚገቡ*** | ***ፍላጎት*** | |
|---|---|---|---|
| | | የነበራቸው | ያልነበራቸው |
| ***መረጃ*** | የነበራቸው | ገጽታ 1 | ገጽታ 3 |
| | ያልነበራቸው | ገጽታ 2 | ገጽታ 4 |

***ስዕል 4*** *ህጻናት ቀንጃ ከመግባታቸው በፊት ቀንጃ እንደሚገቡ የነበራቸው መረጃና ፍላጎት*

## ***መደምደሚያና ይሁንታ***

### ***መደምደሚያ***

ይህ ጥናት የተከናወነው የቀንጃን ምንነትና በህጻናት እድገት ላይ ያለውን አንድምታ ለማወቅ ታቅዶ ነበር። ከዚህ አኳያ ቀንጃ ቀደም ሲልና በአሁኑ ሰዓት ያለበትን ሁኔታ፣ ቀንጃ ከጾታና ከእድሜ ጋር ያለውን ቁርኝት፣ የቀንጃ ውል አያያዝ፣ የቀንጃ አይነቶች እና ቀንጃ ልጆች በቀንጃ ቤት የሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚያጋጥሟቸው ሁኔታዎች በጥናቱ የተዳሰሱ ነጥቦች ናቸው።

በመሆኑም (1) የቀንጃ ሥርዓትን ጥናቱ የተከናወነበት ማህበረሰብ ያሉበትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች ለመፍታት ሲጠቀምበት የቆየ (ወይም እየተጠቀመበት ያለ) መሆኑን፤ (2) ቀንጃ ወንዶች ብቻ የሚገቡበት እና ከህጻናት በተጨማሪ አዋቂዎችም ሊገቡበት እንደሚችሉ፤ (3) ቀንጃ የአካባቢውን ባህላዊ ደንቦችና ህጎች (customary laws) ተንተርሶ የራሱ የውል አያያዝ ሂደት እንዳለው እና (4) ቀንጃ መግባት ለህጻናት እና ለቤተሰቦቻቸው ህልውናና የወደፊት ኑሮ አስፈላጊ መሆኑን (5) ነገር ግን መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች ቀንጃ አስከፊ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ በመሆኑ ሥርዓቱ ሙሉ በሙሉ እንዲቀር የተለያዩ ስራዎችን እያከናወኑ እንደሚገኙ በጥናቱ የቀረቡትን መረጃዎች፣ ትንታኔዎችና ማብራሪያዎች መነሻ በማድረግ ጊዚያዊ ድምዳሜ ላይ መድረሰ ይቻላል።

### ***ይሁንታ***

ይህ ጥናት ይዞ የተነሳውን ዓላማ ከግብ ያደረሰ ቢሆንም ጥናቱ ያልነካካቸው ሶስት መሰረታዊ ነጥቦችን ማንሳት እና ለጥናትና ምርምር ወይም ውይይት ክፍት ማድረግ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው ነጥብ ቀንጃ አስከፊ የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ ነው ወይስ አይደለም ብሎ መበየን ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ አንድቪግ (1998 እ.ኤ.አ) የተጠቀመውን የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ (child labour) ብያኔ ማእቀፎች (defining dimentions) ማንሳትና ቀንጃን ከእነዚህ ነጥቦች አኳያ መፈተሽ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። አንድቪግ እንዳስቀመጠው አስከፊ የህጻናት

ጉልበት ብዝበዛ ሶስት ተያያዥነት ያላቸው ዘርፎችን ያቀፈ ነው። እነርሱም፦


> ... (1) *The properties of the labour process itself*: how hard, unpleasant and dangerous it is, and how many hours the child has to work; (2)... *[the] kind [or characteristics] of monitoring agency the labour is performed under*: whether it is the child's own nuclear family or another domestic unit, whether it is a capitalist firm or a more feudal-like unit that applies some version of forced labour; ... [and] (3) *The degree of responsibility the child has*: particularly

with respect to its own or some of its family members' economic survival. (Andvig, 1998, p.326, emphasis added).

አንድቪግ (1998 እ.ኤ.አ) በጠቀሳቸው መበየኛ መስፈርቶች መሰረት ህጻናት ቀንጃ ከገቡ በኋላ የሚሰሯቸው ስራዎች ዝርዝር ጠባይ (ለምሳሌ፡- ለምን ያህል ሰዓት፣ የት ቦታ)፣ ከተቀባዮች (ከአሰሪዎች) ጋር ያላቸውን ግንኙነት እና ቀንጃ መግባታቸው የሚጥልባቸው የሃላፊነት ደረጃ በአግባቡ መፈተሽ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው ነጥብ ቀንጃ የሚገቡ ህጻናት የሚያከናውኗቸው ስራዎች እና በቀንጃ ቤት የሚደርስባቸው እንግልቶች ወይም እንክብካቤዎች ቀንጃ በመግባታቸው ምክንያት ነው ወይ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም አኳያ እነዚህ ህጻናት *ቢያንስ* ሶስት መለያ ['ለ' ጠብቆ ይነበብ] ባህሪያት ወይም የእድገት ፍላጎቶች (developmental needs) ሊኖሯቸው ይችላል (ስዕል 5)

የመጀመሪያው መለያቸው እነዚህ ህጻናት ቀንጃ በመግባታቸው ያላቸው ፍላጎትና የሚያጋጥማቸው ሁኔታ የተለየ ሊሆን የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩን መገመት ነው፡፡ ሁለተኛው መለያቸው እነዚህ ህጻናት የሚኖሩት ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው (በነበረው) ባህል፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ ነባሪዎች (realities) ውስጥ ነው፡፡ ስለሆነም ከሌሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩ ህጻናት ጋር የሚጋሯቸው ችግሮች፣ ፈተናዎች እና መልካም አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላል፡፡ ለምሳሌ እነዚህ ህጻናት የሚያድጉት በአብዛኛው አዋቂ ተኮር (adult centered) (ፖሉሃ፣ 2004 እ.ኤ.አ)፣ ስራን እንደመደበኛና ትክክለኛ የልጆች ማሳደጊያ ዘዴ በሚጠቀም (ካምፌልድና ይስሃቅ፣ 2011 እ.ኤ.አ) እና ጋርዮሻዊ የቤተሰብ አኗኗር (collective family) (ታጠቅ፣ 2008 እ.ኤ.አ) ዘዬን በሚከተል ማህበረሰብ ወሰጥ በመሆኑ ከሌሎች የኢትዮጵያ ህጻናት ጋር ሊጋሯቸው የሚችሉ ነባሪዎች መኖራቸውን ነው፡፡ በመጨረሻም እነዚህ ህጻናት ልክ እንደማነኛውም በዓለም ላይ እንደሚኖሩ ልጆች ከአዋቂዎች የተለየ ፍላጎት እና እድገቶች እንዳሏቸው መረዳት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ሁለተኛው ነጥብ የሚያመለክተን ቀንጃ የገቡ ልጆች የሚደርስባቸው ብዝበዛ ወይም የሚያገኙት ጥቅም ቀንጃ በመግባታቸው ወይም ቢያንስ ኢትዮጵያ ውስጥ በመኖራቸው የመጣ ስለመሆኑ ለይቶ ማሳየት ሊያስፈልግ ይችላል፡፡




**ስዕል 5** የቀንጃ ህጻናት የእድገት ፍላጎቶች (developmental needs)

ቀንጃ ለልጆች፣ ለላኪ ቤተሰቦችና ለተቀባይ ቤተሰቦች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ እንዳለው የዚህ ጥናት ውጤት በጥቂቱም ቢሆን ጠቁሟል፡፡ ጥናቱ በተጨማሪ እንደጠቆመው ከዚህ በተቃራኒው መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ተቋማት የቀንጃ ሥርዓትን ሙሉ ለሙሉ ለማስቀረት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ ተቋማት እየተከተሉ ያለው ቀንጃን ሙሉ ለሙሉ የማስቀረት አካሄድን (total abolitionist approach) እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ አካሄድ ቀንጃ የሚያስገኛቸው ፋይዳዎችን አብሮ ስለሚያጠፋ ወይም አብረው የሚጠፉትን ፋይዳዎቹን የሚተካ ሌላ ሥርዓት (system) ስካልተካተ ድረስ እነዚህ ተቋማት ይህን አካሄዳቸውን መፈተሽ ያለባቸው ሊሆን ይችላል፡፡

## *ማጣቀሻዎች*


አምሳሉ አክሊሉ፡፡ (2002)፡፡ *አማርኛ-እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት፡፡* 3ኛ እትም፡፡ ማንኩሳ አሳታሚ፣ አዲስ አበባ፡፡

አቢሲኒካ መዝገበ-ቃላት፡፡ (2016 እ.ኤ.አ)፡፡ ከhttp://dictionary.abyssinica.com/ቀንጃ፣ በ18/08/2008 ዓ.ም የተገኘ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (1998) ፡፡ *የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡* አልፋ አታሚዎች (የታተመበት አገር ወይም ቦታ አልተጠቀሰም)፡፡

አብርሃም ሁሴን፡፡ (1996 እ.ኤ.አ) ፡፡ Abraham Husain. (1996). Child rearing practices in the

Siltigna-speaking community: Impacts on the development of independence and social responsibility. In Habtamu Wondimu (Ed.), *Research papers on the situation of children and adolescents in Ethiopia.* Proceedings of the conference on the situation of children and adolescents in Ethiopia, held in Addis Ababa, August 9-10, 1996. (Pp. 136 – 147). Addis Ababa.

አንድቪግ። (1998 እ.ኤ.አ)። Andvig, J. (1998). Child labour in Sub-Saharan Africa – An exploration. *Forum for Development Studies*, 2, 327–362.

አሰፋ አድማሴ እና በዲ። (2003 እ.ኤ.አ)። Admassie & Bedi, A. (2003). Attending school, two 'Rs' and child work in rural Ethiopia. ISS Working Papers - General Series, International Institute of Social Studies of Erasmus University, Rotterdam

አያሌው ዱሬሳ። (2002 እ.ኤ.አ)። Ayalew Duressa. (2002). Guddifachaa: adoption practice in oromo society with particular reference to the borana Oromo. Unpublished Master's Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.

ቤክስትሮም። (1972 እ.ኤ.አ)። Beckstrom, J. (1972). Adoption in Ethiopia ten years after the civil code. *Journal of African Law,* 16 (2), 145-168.

በላይ ተፈራና አብዲናስር አህመድ። (2015 እ.ኤ.አ)። Belay Tefera & Abdinasir Ahmed. (2015). *Research Methods*. Addis Ababa: Mega Printing Press.

በላይ ተፈራና መብራቱ በላቸው። Belay Tefera & Meberate Belachew. (In press). Care and support of orphaned children with adera, non-adera and institutional care arrangements in Debre Markos and Bahir Dar Towns. *Journal of Edcation for Develoment*.

በላይ ተፈራ። (2007 እ.ኤ.አ)። Belay Tefera. (2007). Raising AIDS orphaned children in Ethiopia: Practices of care and support challenges, and future directions. In Belay Tefera & Abebaw Minaye (Eds.), *Caring for orphan and vulnerable children in Ethiopia*. Proceedings of the 6th National Conference of the Ethiopian Psychologists' Association. (Pp. 60-112). Addis Ababa.

ካምፊልድ እና ይሳቅ ታፈረ። (2011 እ.ኤ.አ)። Camfield, L. & Yisak Tafere. (2011). Community understandings of childhood transitions in Ethiopia: Different for girls? *Children's Geographies, 9*(2), 247-262. doi: 10.1080/14733285.2011.562385

ደሳለኝ ነገሪ። (2006 እ.ኤ.አ)። Dessalegn Negari. (2006). Guddifachaa practice as child problem intervention in Oromo society: The case of Ada'a Liban district. Unpublished Master's Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.

ጌትነት ሃይሌ እና በልዩ ሃይሌ። (2012 እ.ኤ.አ)። Getinet Haile & Beliyou Haile. (2012). Child labour and child schooling in rural Ethiopia: Nature and trade-off. Education Economics, 20(4), 365-385. doi: 10.1080/09645292.2011.623376

ግዛቸው በላይነህ። (ታህሳስ፣ 7፣ 2012 እ.ኤ.አ.)። ቀንጃ ህፃንነት ለአካልና አዕምሮአዊ ዕድገት ወይስ ገቢ ለማስገኘት። ከ WordPress.com፣ በ18/08/2008 ዓ.ም የተገኘ።

ማይልስ እና ሁበር ማን። (1994 እ.ኤ.አ)። Miles, M. & Huberman, A. (1994). *An extended sourcebook: Qualitative data analysis*. 2nd ed. Thousand Oaks: Sage.

ኦርኪን። (2010 እ.ኤ.አ)። Orkin, K. (2010). In the child's best interests? Legislation on children's work in Ethiopia. *Journal of International Development, 22*(8), 1102-1114. doi: 10.1002/jid.1749

ኦርኪን። (2012 እ.ኤ.አ)። Orkin, K. (2012). Are work and schooling complementary or competitive for children in rural Ethiopia? A mixed-methods study. Young Lives, WORKING PAPER NO. 77. www.younglives.org.uk

ፓፓሊያ እና ኦልድስ ። (1990 እ.ኤ.አ)። Papalia, D. & Olds, S. (1990). *A child's world: Infancy*

*through adolescence*. 5th ed. United States of America: McGrow-Hill.

ፓተን። (2002 እ.ኤ.አ)። Patton, M**.** **(**2002**).** *Qualitative research and evaluation*. 3rd ed. Sage Publication.

ፖሉሃ። (2004 እ.ኤ.አ)። Poluha, E. (2004). *The power of continuity: Ethiopia through the eyes of its children*. Uppsala: Nordic African Institute.

ፖሉሃ። (2007 እ.ኤ.አ)። Poluha, E. (2007). Research on Ethiopian children: Subjects covered and possible new themes. In E. Poluha (Ed.), The world of girls and boys in rural and urban Ethiopia (Pp. 158-181). Addis Ababa: Forum for Social Studies in association with Save the children.

ሲምስ እና ስቴፈንስ። (2005 እ.ኤ.አ)። Sims, M & Stephens, M. (2005). *Living folklore: An introduction to the study of people and their traditions.* United States of America: Utah State University.

ሶፍያ ጫንያለው እና ታጠቅ አበበ ። (2016 እ.ኤ.አ)። Sophia Chanyalew & Tatek Abebe. (2016). Qenja: child fostering and relocation practices in the Amhara region, Ethiopia. *Children's Geographies, 14*(1), 46-62. doi:10.1080/14733285.2014.974508

ታጠቅ አበበ። (2008 እ.ኤ.አ)። Tatek Abebe. (2008). *Ethiopian childhoods: A case study of the lives of orphans and working children* (Unpublished doctoral dissertation). Norwegian University of Science and Technology, Norway.

ታጠቅ አበበ። (2010 እ.ኤ.አ)። Tatek Abebe (2010). Trapped between disparate worlds? The livelihoods, socialisation and school contexts of rural children in Ethiopia.

ይግዛው ሃይሌ። (2009እ.ኤ.አ)። Yigzaw Haile. (2009). Practice and contributions of Adera in caring and supporting of orphaned and vulnerable children: The case of Alamata Town. Unpublished Master's Thesis, Addis Ababa University, Addis Ababa.

---

[i] እ.ኤ.አ ማለት እንደ ኤሮፓውያን (ወይም ጎርጎሮሳውያን) አቆጣጠር ነው። በዚህ ጽሁፍ ቃሉ ወይም ሀረጉ በአማርኛ ተጽፎ ይህ ማሳጠሪያ አብሮ ወይም ከጎን ተቀመጠ የምንጩ ህትመት ጊዜ በጎርጎሮሳውያን የዓመት አቆጣጠር (calendar) ሥርዓት መሆኑን የሚያመለክት ሲሆን ማሳጠሪያው ያልተጠቀሰባቸው ሁሉም ዓመቶች የኢትዮጵያን የአቆጣጠር ስልት የተከተሉ ናቸው። ነገር ግን በእንግሊዝኛ በተጻፉ የደራሲ ስሞች በሙሉ ይህ ማሳጠሪያ ባይጠቀስም አቆጣጠሩ እንደጎርጎሮሳውያን ነው።

[ii] ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ ሂደት ከፍተኛ ድጋፍ ያደረጉልንን አቶ አንማው ተፈራን እናመሰግናለን።

[iii] ተከርቸም ማለት ወንድ (ባል) ከሴት (ሚስት) ወላጆች ጋር አብሮ በመኖር ወይም ወንድ (ባል) ሴት (ሚስት) ወደ ግል ቤት በመሄድ ትዳር የሚመሰረትበት ሥርዓት ነው።

[iv] ቃለ መጠይቅ የተደረገለት የዚህ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ተወካይ መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ ለአንደኛው አጥኚ በስልክ ደውሎ የድርጅቱ ስም ሪፖርት ሲጻፍ እንዳይገለጽ በማለቱ ነው ስሙ ያልተጠቀሰው።